# ክ ፍ ል – ሁ ለ ት

## ጌታን በተቀበልንበት ጊዜ በሕይወታችን የተፈጸሙ ተስፋዎች

ከዚህ ቀጥሎ በክፍል ሁለት፤ ሦስት፤ አራትና አምስት የምንዘረዝራቸው ተስፋዎች ለክርስቲያኖች የተሰጡ ተስፋዎች ናቸው። ስለዚህ የጌታ ልጅ ከሆንክ እነዚህን ተስፋዎች በቃል ኪዳን ከጌታ የተሰጡህ ናቸውና በእምነት የራስህ አድርጋቸው። ጌታ ከገባቸው ተስፋዎች ብዙዎቹ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ ግል አዳኛችን አድርገን በተቀበልን ጊዜ ተፈጽመዋል፤ ወይም የእኛ ሆነዋል። ክርስቲያን እነዚህን በረከቶች የእርሱ መሆናቸውን እንደ ጌታ ቃል ለእግዚአብሔር ክብር፤ ለሕይወቱ ዕድገትና ለሌሎች መታነጽ እንዲሆን በእምነት ወስዶ ከመጠቀም በስተቀር ሌላ ምንም ማድረግ አይኖርበትም። ከዚህ ቀጥሎ ከደህንነታችን ጋር ስለ ተሰጡንና በምስጋና ተቀብለን ልንለማመዳቸው ወይም ልንኖርባቸው ስለሚገቡን ተስፋዎች ከጌታ ቃል አንጻር ለማየት እንሞክራለን፤

### 1. የእግዚአብሔር ልጅ ሆነሃል

"ለተቀበሉት ሁሉ ግን፤ በስሙ ለሚያምኑ ለእነርሱ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው፤" (ዮሐ. 1፡12)

ከደህንነታችን ውጤት አንዱ የእግዚአብሔር ልጅ መሆን ነው። ክርስቶስን ለተቀበሉ ሁሉ የልጅነት ሥልጣን ተሰጥቷቸዋል። ልጅነት የአንድነት ወይም የቅርበት መግለጫ ስም ነው። ልጅነት ከሁሉ በላይ የቀረበ ግኑኝነት መሆኑን አንዱ ማረጋገጫው ጌታ ኢየሱስ ሥጋ ለብሶ ወደ ዓለም በመጣ ጊዜ የእግዚአብሔር ልጅ ተብሎ መጠራቱ ነው።

ልጅነት ከሁሉም በላይ የሆነ ታላቅ የማዕረግ ስም ብቻ ሳይሆን የአማኙን መብትና ማንነት የሚገልጽ ነው። ይህ የልጅነት ስም ለክርስቲያኖች ሁሉ የሚከተሉትን ያረጋግጥላቸዋል።

1.1 ማንም የማይወዳደረው ግኑኝነት ከአምላካቸው ጋር እንዳላቸው።

1.2 ከሁሉም የበለጠ ማዕረግ (በሰማይም በምድርም) እንደተሰጣቸው።

1.3 በሕብረት ላይ የተመሠረተ ሥልጣን እንዳላቸው።

1.4 የውርስ መብት እንደተሰጣቸው።

1.5 በእግዚአብሔር ቤት ለዘላለም እንደሚኖሩ።

1.6 ከመላዕክትም በላይ እግዚአብሔር ከፍ እንዳደረጋቸው።

1.7 ለአዳም እንኳን ያልተሰጠ ግኑኝነት እንዳላቸው።

## የውይይት መነሻ ጥያቄዎች

1. የልጅነት በረከቶች ምንድን ናቸው?

- ________________
- ________________
- ________________
- ________________
- ________________

2. የልጅነት መብትህን ዘርዝር?

- ________________
- ________________
- ________________
- ________________
- ________________

3. የልጅነት ኃላፊነቶች ምንድን ናቸው?

- ________________
- ________________
- ________________
- ________________
- ________________

## 2. የዘላለም ሕይወት ተሰጥቶሃል

"እግዚአብሔርም የዘላለምን ሕይወት እንደ ሰጠን ይህም ሕይወት በልጁ እንዳለ ምስክሩ ይህ ነው።" (1ዮሐ. 5፥11)

"... እኔም የዘላለምን ሕይወት እሰጣቸዋለሁ ለዘላለምም አይጠፉም፤ ከእጄም ማንም አይነጥቃቸውም።" (ዮሐ. 10፥28)

"...የእግዚአብሔር የጸጋ ስጦታ ግን በክርስቶስ ኢየሱስ በጌታችን የዘላለም ሕይወት ነው።" (ሮሜ. 6፥23)

"በልጁ የሚያምን የዘላለም ሕይወት አለው..." (ዮሐ. 3፥36)

በዮሐንስ ወንጌል (3፥16፤ 4፥14፤ 5፥24፤ 6፥68፤ 10፥28) እና በ1ኛ ዮሐንስ ውስጥ ብቻ እንኳን በክርስቶስ ኢየሱስ ያመነ ሰው የዘላለም ሕይወት እንዳለው 12 ጊዜ ተጠቅሷል። የዘላለም ሕይወት መቀበል ማለት፦

2.1 ከመንፈሳዊ ሞት ወደ ሕይወት መሸጋገር (ኤፌ. 2፥2) ማለት ነው።

2.2 የሕይወትን መንፈስ ለማግኘት ከእግዚአብሔር ጋር ተቋርጦ የነበረው ግኑኝነት ማደስና (ኤፌ.2፥5) እንዲሁም፤

2.3 የእግዚአብሔርን ሕይወት መቀበል ማለት ነው።

ይህ የማይሞት፤ የማይለወጥ ዘላለማዊ የሆነ የእግዚአብሔር ሕይወት ስለሆነ የእግዚአብሔር ልጅ የሆነ ሁሉ የእግዚአብሔር ሕይወት አለው ማለት ነው። ስለዚህ የጌታ ሕይወት ያለው ሁሉ እንዲሁ በታሪክ ውስጥ የሚያልፍ ሰው ሳይሆን ዓላማ፤ ግብ፤ የዘላለም ሕይወት፤ ዋስትናና ደስታ አለው። ክርስቲያን የዘላለምን ሕይወት አይጠብቅም ዘላለማዊ የሆነ የእግዚአብሔር ሕይወት አለው። ሞትና ሲኦል በእርሱ ላይ ኃይል የላቸውም ማለት ነው። ይህም በመሆኑ በድፍረትና በሥልጣን ይኖራል። የእግዚአብሔር ሕይወት የማይጠፋና ማንም ሊወስድብን የማይችል እውነተኛ ሀብት ነው።

## የውይይት መነሻ ጥያቄዎች

1. የዘላለም ሕይወት ያለው ሰው ከሌላው በምን ይለያል?

- ◆
- ◆
- ◆
- ◆
- ◆

2. የዘላለም ሕይወት ጥቅም ምንድነው?

- ◆
- ◆
- ◆
- ◆
- ◆

3. ለምድራዊ ኑሮ ምን ጥቅም አለው?

- ◆
- ◆
- ◆
- ◆
- ◆

4. ሰው የዘላለም ሕይወት እንዳለው እንዴትና በምን እርግጠኛ መሆን ይችላል?

- ◆
- ◆
- ◆
- ◆
- ◆

## 3. የኃጢያት ይቅርታ ተሰጥቶሃል

አንድ ሰው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ ግል አዳኙ በተቀበለ ጊዜ የኃጢያት ይቅርታን ይቀበላል። ስለሆነም የሚከተሉት አሥራ አምስት ውጤቶች በሕይወቱ ውስጥ ተፈጽመዋል ማለት ነው፡-

3.1 ከኃጢያቱ በክርስቶስ ደም ነጽቷል። "ነገር ግን እርሱ በብርሃን እንዳለ በብርሃን ብንመላለስ ለእያንዳንዳችን ኅብረት አለን፤ የልጁም የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከኃጢያት ሁሉ ያነጻናል።" (1ዮሐ. 1፡7)

3.2 በክርስቶስ ደም ጸድቋል። (ሮሜ 5፡9)

3.3 በክርስቶስ ደም ከእግዚአብሔር ቁጣ ድኗል። "ይልቁንስ እንግዲህ በደሙ ከጸደቅን በእርሱ ከቁጣው እንድናለን።" (ሮሜ 5፡9)

3.4 ይቅርታ ተቀብሏል። "በደላችሁን ሁሉ ይቅር አላችሁ" (ቆላ. 2፡13) "ኃጢአትሽን ሁሉ ይቅር የሚል ..." (መዝ. 102፡3)

3.5 ኃጢአቱን ሁለተኛ እንደማይገኝ አድርጎ አርቆታል። "...በዚያን ወራት በዚያም ዘመን፤ ይላል እግዚአብሔር የእስራኤል በደል የይሁዳም ኃጢአት ይፈለጋል ምንም አይገኝም።" (ኤር. 50፡20)

3.6 ኃጢአቱን ወደ ባህር ጥልቅ ጥሎታል። "ተመልሶ ይምረናል ክፋታችንንም ይጠቀጥቃል፤ ኃጢአታችንንም በባሕሩ ጥልቅ ይጥለዋል።" (ሚክ. 7፡19)

3.7 ኃጢአቱን ወደ ኋላው ጥሎለታል። "እነሆ ታላቅ ምሬት ለደህንነቴ ሆነ፤ አንተም ነፍሴን ከጥፋት ጉድጓድ አዳንሃት፤ ኃጢአቴንም ሁሉ ወደ ኋላህ ጣልህ።" (ኢሳ. 38፡17)

3.8 የሚከሰውን የኃጢአት ክስ ሽሮለታል። "በእኛ ላይ የነበረውን የሚቃወመንን በትዕዛዛት የተጻፈውን የዕዳ ጽሕፈት ደመሰሰው።" (ቆላ. 2፡14)

3.9 በእግዚአብሔር ፊት ያለነቀፋ ሆኗል። "ዓለም ሳይፈጠር፤ በፊቱ ቅዱሳንና ነውር የሌለን በፍቅር እንሆን ዘንድ በክርስቶስ መረጠን።" (ኤፌ. 1፡4)

3.10 ከበደሉ እንደ በረዶ ነጽቷል። "ኑና እንዋቀስ ይላል እግዚአብሔር ኃጢአታችሁ እንደ አለላ ብትሆን እንደ አመዳይ ትነጻለች እንደ ደምም ብትቀላ እንደ ባዘቶ ትጠራለች።" (ኢሳ. 1፡18)

3.11 እግዚአብሔር ኃጢአቱን ደግሞ አያስብበትም። "መተላለፍህን ስለ እኔ ስል የምደመስስ እኔ ነኝ፤ ኃጢአትህንም አላስብም።" (ኢሳ. 43፡25)

3.12 እግዚአብሔር ኃጢአቱን ከእርሱ አርቆለታል። "ምሥራቅ ከምዕራብ እንደሚርቅ፤ እንዲሁ ኃጢአታችንን ከእኛ አራቀ።" (መዝ. 102፡12)

3.13 ሊከሰው የሚችል የለም። "እግዚአብሔር የመረጣቸውን ማን ይከሳቸዋል? የሚያጸድቅ እግዚአብሔር ነው የሚኮንንስ ማን ነው?" (ሮሜ 8፡33)

3.14 ከኩነኔ ከኃጢአት ፍርድ ነጻ ሆኗል። "እንግዲህ በክርስቶስ ኢየሱስ ላሉት አሁን ኩነኔ የለባቸውም።" (ሮሜ. 8፡1)

3.15 እግዚአብሔር ኃጢአቱን አይቆጥርበትም። "እግዚአብሔር በደልን የማይቆጥርበት በመንፈሱም ሽንገላ የሌለበት ሰው ምስጉን ነው።" (መዝ. 31፡2)

ስለዚህ የኃጢአት ይቅርታ ያገኘ ሰው ሁሉ ምንም ኃጢአትን እንዳላደረገ ሆኖ በእግዚአብሔር ፊት ሊቆም ይችላል። ሰው የተናዘዘውን ኃጢአት እግዚአብሔር ይቅር ካለ በኋላ ከመዝገቡ ፍጻውን እንደሚፍቅ በዳዊት ሕይወት ውስጥ እናያለን። ዳዊት ኃጢአት በሠራ ጊዜ እግዚአብሔር ነቢዩ ናታንን ልኮ ስለዚህ ጉዳይ ዳዊትን ገሠጸው። ዳዊት ንስሐ ገብቶ

ኃጢአቱን ተናዘዘ። (መዝ. 51) ጌታም ይቅር አለው። ይህ የተጻፈው በ2ኛ ሳሙኤል ውስጥ ሲሆን፤ የዳዊት ታሪክ እንደገና በ1ኛ ዜና መዋዕል ውስጥ ሲደገም በእነዚህ በተጻፉት ሁለት መጻሕፍት መካከል አንድ ትልቅ ልዩነት እንዳለ በግልጽ ይታያል። ይኸውም በ1ኛ ዜና መዋዕል ውስጥ የዳዊት ኃጢአት ዳግመኛ አለመገለጡ ነው። ዳዊት በተናዘዘ ጊዜ ኃጢአቱ ይቅር ስለተባለለት ጌታ ቀደም ብሎ የፈጸመውን በደሉን ሁለተኛ በመዝገቡ አልጻፈውም። ለእግዚአብሔር ልጆች ይህን ማወቅና ማመን እጅግ ይጠቅማል። ሰይጣንም ከሚያመጣባቸው የሐሰት ክስ በነፃነት ሆነው ያለ ፍርሃት እንዲኖሩ ያስችላቸዋል።

## የውይይት መነሻ ጥያቄዎች

1. የኃጢአት ይቅርታ የተቀበለ ሰው በምን ይታወቃል?

- ______
- ______
- ______
- ______
- ______

2. እግዚአብሔር ኃጢአትን እንደሚጠላ በምን እናውቃለን?

- ______
- ______
- ______
- ______
- ______

3. ይቅርታን በመስጠትና በመቀበል መካከል ምን ግንኙነት አለ? (ማቴ. 6:9-11)

- ______
- ______
- ______
- ______
- ______

4. ይቅር ማለት ጥቅሙ ምንድነው? ለማንስ ነው?

- ______
- ______
- ______
- ______

5. ይቅር አለ ማለት ጉዳቱ ምንድነው?

- 
- 
- 

## 4. አዲስ ፍጥረት ሆነሃል

"ስለዚህ ማንም በክርስቶስ ቢሆን አዲስ ፍጥረት ነው፤ አሮጌው ነገር አልፎአል፤ እነሆ ሁሉም አዲስ ሆኗል።" (2ቆሮ. 5፡17)

ሰው ጌታን ተቀብሎ በክርስቶስ መሆን ሲጀምር በጥቂቱ ብቻ አይሻሻልም፤ ነገር ግን ፍጹም ይለወጣል። ይህ ከዳግም ልደት የሚገኝ ፍጹም መለወጥ ነው። (ዮሐ. 3፡15) ከዚህ የተነሣ አዲስ ሰው ይሆናል። እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ በሕይወታችን ውስጥ ሁሉንም ነገር አዲስ ስለ አደረገ ያለፈውን ነገር ወደ ኋላ በመተው አዲስ ጉዞ ከጌታ ጋር እንጓዛለን። እነሆ ሁሉንም አዲስ ያደረገው ጌታም፤ ስላለፈው ነገር ማሰላሰል ትተን በአዲሱ ሕይወት እንድንኖር ይጠይቀናል። "የፊተኛውን ነገር አታስተውሉ፤ የጥንቱንም ነገር አታስቡ። እነሆ አዲስ ነገርን አደርጋለሁ፤ እርሱም አሁን ይበቅላል፤ እናንተም አታውቁትም? በምድረበዳም መንገድን በበረሃም ወንዞችን አደርጋለሁ።" (ኢሳ. 43፡18–19) አንድ ቀን ደግሞ ሕይወታችንን ብቻ ሳይሆን ሁሉንም ነገር ደግሞ አዲስ ያደርጋል። ከእንግዲህ ወዲህ ሌሊት አይሆንም፤ ጌታ አምላክም በእነርሱ ላይ ያበራላቸዋልና የመብራት ብርሃንና የፀሐይ ብርሃን አያስፈልጋቸውም፤ ለዘላለም እስከ ዘላለም ይነግሣሉ። ራዕይ 21 ተመልከት።

### የውይይት መነሻ ጥያቄዎች

1. በመለወጥና እየተሻሻሉ በመሄድ መካከል ምን ልዩነትና ግንኙነት ያለ ይመስልሃል?

- 
- 
- 
- 
- 

2. መለወጥ የዕድገት መሠረት ለምን ሆነ?

- ________________
- ________________
- ________________
- ________________

## 5. ስምህ በሕይወት መጽሐፍ ተጽፎአል

"ነገር ግን መናፍስት ስለ ተገዙላችሁ በዚህ ደስ አይበላችሁ፣ ስማችሁ ግን በሰማያት ስለ ተጻፈ ደስ ይበላችሁ" (ሉቃ. 10፡20)

ስማቸው በሕይወት መዝገብ ያልተጻፈ ሁሉ በፍርድ ቀን ወደ ዘላለማዊው እሳት ይጣላሉ። "በሕይወትም መጽሐፍ ተጽፎ ያልተገኘው ማንኛውም በእሳት ባሕር ውስጥ ተጣለ።" (ራዕ. 20፡15) ስለዚህ በክርስቶስ የሕይወት መዝገብ ውስጥ መጻፍ የዘላለም ሕይወት እንዳለን የሚያረጋግጥ ታላቅ ዋስትና ነው። (ሉቃ. 10፡20) ጌታ ኢየሱስ የደሙን ዋጋ ከፍሎበት በሕይወት መዝገብ የጻፈውን ሰው ስም ሊፍቅ የሚችል ምንም ኃይል እንደሌለ ይህ መዝገብ ለክርስቲያን ታላቅ እረፍት ከመሆኑም በላይ በፍርሃትና በአክብሮት ይህን ላደረገልን ጌታ እንድንኖር መለኮታዊ ፍቅሩ ያስገድደናል። "ይህን ስለ ቆረጥን የክርስቶስ ፍቅር ግድ ይለናልና አንዱ ስለ ሁሉ ሞተ እንግዲያስ ሁሉ ሞቱ በሕይወትም ያሉት ስለ እነርሱ ለሞተውና ለተነሣው እንጂ ወደ ፊት ለራሳቸው እንዳይኖሩ ስለ ሁሉ ሞተ።" (2ቆሮ. 5፡14)

### <u>የውይይት</u> መነሻ <u>ጥያቄዎች</u>

1. ስማችን በሕይወት መዝገብ የመጻፉ ትልቅነት ምኑ ላይ ነው?

- ________________
- ________________
- ________________
- ________________
- ________________

2. በእግዚአብሔር ስም የመጠራታችን ኃላፊነት ምንድን ነው?

- ◆ ________________
- ◆ ________________
- ◆ ________________
- ◆ ________________
- ◆ ________________

## 6. በመንፈስ ቅዱስ ማህተም ታትመሃል

"እናንተም ደግሞ የእውነትን ቃል፤ ይኸውም የመዳናችሁን ወንጌል ሰምታችሁ ደግሞም በክርስቶስ አምናችሁ፤ በተስፋው መንፈስ በመንፈስ ቅዱስ ታተማችሁ።" (ኤፌ. 1፡13)

### የማህተም አስፈላጊነቱ የሚከተሉትን ለማረጋገጥ ነው:-

6.1 የንብረቱ ባለቤት ማን መሆኑን ያረጋግጣል። የመንፈስ ቅዱስ ማህተም ያለበት ሁሉ የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ንብረት ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ "እኔ የኢየሱስን ማህተም በሥጋዬ ተሸክሜአለሁና ከእንግዲህ ወዲህ አንድ ስንኳ አያደክመኝም።" (ገላ. 6፡17) የሚለው ለዚህ ነው።

6.2 በመለኮታዊ ኃይል የተጠበቀ ንብረት ሁሉ የጌታ ስለሆነ ማንም ቢሆን ምንም ሊያደርገው አይችልም። የመንፈስ ቅዱስ ማህተም ያለበት ሰው ሁሉ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል የተጠበቀ ነው።

6.3 ማህተም ስለማይፋቅ ቋሚነት አለው። የመንፈስ ቅዱስን ማህተም ሊፍቅ የሚችል ስለሌለ ክርስቲያን በምስጋና ተሞልቶ ለአምላክ ክብር መኖር ይችላል።

6.4 ማህተም ንብረቱ የተከበረ መሆኑን ያረጋግጣል። እግዚአብሔር የመንፈሱን ማህተም በእኛ ላይ ሲያኖር በታላቅ አክብሮት አክብሮናል። የእርሱ በመሆናችን አያፍርብንም።

## የውይይት መነሻ ጥያቄዎች

1. የደህንነታችን ዋስትናዎች ምንድን ናቸው?

- 
- 
- 
- 
- 

2. ይህን መረዳት ለሕይወትና ለአገልግሎት እንዴት ይረዳል?

- 
- 
- 
- 
- 

# 7. እግዚአብሔር አባት ሆኖልሃል

"አባ አባት ብለን የምንጮህበትን የልጅነት መንፈስ ተቀበላችሁ እንጂ እንደገና ለፍርሃት የባርነት መንፈስ አልተቀበላችሁምና።" (ሮሜ 8፡15)

"ልጆችም ስለሆናችሁ እግዚአብሔር አባ አባት ብሎ የሚጮህ የልጁን መንፈስ በልባችሁ ውስጥ ላከ።" (ገላ. 4፡6)

ሁሉን የሚችልና ስለፍጥረታችን ሁሉንም ነገር የሚረዳ እግዚአብሔር አባት ሆኖሃል። ይህ በጣም ጥልቀት ያለው ሕብረት ወይም አንድነት ነው። እግዚአብሔር ፈጣሪህና አዳኝህ ብቻ ሳይሆን አባትም ሆኖሃል። በአዲስ ኪዳን ውስጥ ብቻ 250 ጊዜያት እግዚአብሔር አባታችን እንደሆነ ተጠቅሷል። መጽሐፍ ቅዱስን ስንመረምር የምድራዊ አባትነት ሃላፊነትን እንደሚከተለው ይዘረዝራል፦

7.1 ቤተሰቡን እያስተማረ በጽድቅ መንገድ ይመራል። (ዘፀ. 12፡3፤ 13፡14–16፤ ዘዳግ. 6፡4–9 ኢሳ. 38፡19) እግዚአብሔር ለልጆቹ እንዲሁ

ያደርጋል። ይህም በመሆኑ ነው መንፈስ ቅዱስን አስተማሪያችን እንዲሆን የላከው።

7.2 ቤተሰቡን ልጆቹን ይመክራል፦ "ልጄ ሆይ፣ ስማ ጠቢብም ሁን፤ ልብህንም በቀና መንገድ ምራ። የወለደህን አባትህን ስማ፣ እናትህን ባረጀች ጊዜ አትናቃት።" (ምሳ. 23፡19፤22) እግዚአብሔር ልጆቹን በምክር ይመራል፤ ያሳድግማል። ጌታ ኢየሱስ ድንቅ፣ መካር የዘላለም አባት፤ የተባለው ይህን ግልጽ ሊያደርግልን ነው።

7.3 አባት ቤተሰቡን ይጠብቃል። መልካም አባት ለቤተሰቡ መልካምና ቸል የማይል ዘበኛ ነው። (የእግዚአብሔርን ጥበቃ ተመልከት)

7.4 አባት ለቤተሰቡ የዕለት ምግባቸውን፤ የሚኖሩበትን፤ የሚለብሱትንና በአጠቃላይ የሚያስፈልጋቸውን ሁሉ ለማዘጋጀት የማያቋርጥ ጥረት ያደርጋል። እግዚአብሔር ደግሞ ለሕዝቡ ከዚያ የበለጠ ጥንቃቄን ያደርግላቸዋል። "ሁሉንም የሚገዛ ጌታ፤ እኔም እቀበላችኋለሁ፤ ለእናንተም አባት እሆናለሁ እናንተም ለእኔ ወንድ ልጆችና ሴት ልጆች ትሆናላችሁ ይላል።" (2ቆሮ. 6፡18)

7.5 አባት ለልጆቹ ይራራል። "አባት ለልጆቹ እንደሚራራ እንዲሁ እግዚአብሔር ለሚፈሩት ይራራል።" (መዝ. 102፡13)

7.6 አባት የሚወደውን ልጁን ሲያስፈልግ ከምክርም አልፎ ይቀጣል፤ ይገስጻል። "እግዚአብሔር እንደ ልጆች ያደርግላችኋልና አባቱ የማይቀጣው ልጅ ማን ነው? ነገር ግን ሁሉ የቅጣት ተካፋይ ሆኖአልና ያለ ቅጣት ብትኖሩ ዲቃላዎች እንጂ ልጆች አይደላችሁም። ከዚህም በላይ የቀጡን የሥጋችን አባቶች ነበሩን እናፍራቸው ነበር፤ እንዴትስ ይልቅ ለመናፍስት አባት አብልጠን ልንገዛና በሕይወት ልንኖር በተገባን? እነርሱ መልካም ሆኖ እንደታያቸው ለጥቂት ቀን ይቀጡን ነበርና፣ እርሱ ግን ከቅድስናው እንድንካፈል ለጥቅማችን ይቀጣናል። ቅጣት ሁሉ ለጊዜው የሚያሳዝን እንጂ

ደስ የሚያሰኝ አይመስልም፤ ጻሩ ግን በኋላ ለለመዱት የሰላምን ፍሬ እርሱም ጽድቅን ያፈራላቸዋል።" (ዕብ. 12፡7–11)

7.7 መልካም አባት ቤተሰቡን እንደሚወድ ሁሉ፣ እግዚአብሔርም ልጆቹን እንዲሁ ይወዳል። "የእግዚአብሔር ልጆች ተብለን ልንጠራ አብ እንዴት ያለውን ፍቅር እንደ ሰጠን እዩ እንዲሁም ነን። ስለዚህ ምክንያት ዓለም እርሱን ስላላወቀው እኛን አያውቀንም።" (1ዮሐ. 3፡1) እንዲሁም የይሁዳ መጽሐፍን ተመልከት።

7.8 መልካም አባት ልጆቹን እንደሚሰማቸው እንዲሁ እግዚአብሔርም ይሰማናል። "አንተ ግን ስትጸልይ፤ ወደ እልፍኝህ ግባ መዝጊያህንም ዘግተህ በስውር ላለው አባትህ ጸልይ በስውር የሚያይ አባትህም በግልጥ ይከፍልሃል።" (ማቴ. 6፡6፤ 18፡19)

7.9 መልካም አባት ስለሆነ የሚያስፈልገንን ያውቃል። "ስለዚህ አትምሰሉአቸው፤ ሳትለምኑት የሚያስፈልጋችሁን ያውቃልና።" (ማቴ. 6፡8፤ ሉቃ. 12፡30)

7.10 መልካም ስጦታን ይሰጠናል "ወይስ ከእናንተ ልጁ እንጀራ ቢለምነው ድንጋይ የሚሰጠው ከእናንተ ማን ሰው ነው? ዓሣስ ቢለምነው እባብ ይሰጠዋልን እንኪያስ እናንተ ክፉዎች ስትሆኑ ለልጆቻችሁ መልካም ስጦታን መስጠትን ካወቃችሁ በሰማያት ያለው አባታችሁ ለሚለምኑት እንዴት አብልጦ መልካም ነገርን ይሰጣቸው?" (ማቴ. 7፡11፤ ሉቃ. 11፡13)

7.11 እግዚአብሔር የሚጠነቀቅልን አባት ስለሆነ ስማችንንና መልካችንን ብቻ ሳይሆን የራሳችንንም ጸጉር ብዛት እንኳ ሳይቀር ያውቃል። "የእናንተስ የራሳችሁ ጠጉር ሁሉ እንኳ ተቆጥሮአል። እንግዲህ አትፍሩ ከብዙ ድንቢጦች እናንተ ትበልጣላችሁ።" (ማቴ. 10፡30)

<u>የውይይት መነሻ ጥያቄዎች</u>

1. ስለ እግዚአብሔር አባትነት ምን ትላለህ?

- 
- 
- 
- 
- 

2. የአባትነቱ በረከቶች ምንድን ናቸው?

- 
- 
- 
- 
- 

3. አባትነቱን መቀበል የሚያስከትለውን ሃላፊነት ዘርዝር።

- 
- 
- 
- 
- 

## 8. ከሞት ወደ ሕይወት ተሻግረሃል

"እውነት እውነት እላችኋለሁ፤ ቃሌን የሚሰማ የላከኝንም የሚያምን የዘላለም ሕይወት አለው፤ ከሞት ወደ ሕይወት ተሻገረ እንጂ ወደ ፍርድ አይመጣም።" (ዮሐ. 5፡24)

"በበደላችሁና በኃጢያታችሁ ሙታን ነበራችሁ፤...ነገር ግን እግዚአብሔር በምሕረቱ ባለጠጋ ስለሆነ ከወደደን ከትልቅ ፍቅሩ የተነሣ በበደላችን ሙታን እንኳ በሆንን ጊዜ ከክርስቶስ ጋር ሕይወት ሰጠን፤ ..." (ኤፌ. 2፡1፤ 4–5)

## የውይይት መነሻ ጥያቄዎች

1. መሻገር የሚለውን ሃሳብ ከመንፈሳዊ አንጻር መረዳት ለምን ያስፈልጋል?

- 
- 
- 
- 

2. ከሞት ወደ ሕይወት ከመሻገር ሌላ በዕለታዊ ኑሮ ውስጥ የምንሻገራቸው ነገሮች ምንድን ናቸው?

- 
- 
- 
- 

3. ቀይ ባሕርን እንደ ተሻገሩ ዮርዳኖስንም ተሻገሩ። ለክርስትና ሕይወት ምሳሌነታቸው ምንድነው?

- 
- 
- 
- 

# 9. ለኃጢአት ሞተህ ለጽድቅ ተነስተሃል

"በክርስቶስ ኢየሱስ ለእኛ ባለው ቸርነት ከሁሉ የሚበልጠውን የጸጋውን ባለጠግነት ያሳይ ዘንድ ከእርሱ ጋር አስነሣን በክርስቶስ ኢየሱስም በሰማያዊ ሥፍራ ከእርሱ ጋር አስቀመጠን።" (ኤፌ. 2፡7)

9.1 ከክርስቶስ ጋር ተነሥተሃል። "እንግዲህ ከክርስቶስ ጋር ከተነሣችሁ ክርስቶስ በእግዚአብሔር ቀኝ ተቀምጦ በአለበት በላይ ያለውን እሹ፤ በላይ ያለውን አስቡ እንጂ በምድር ያለውን አይደለም።" (ቆላ. 3፡1–2) "ሞቱን በሚመስል ሞት ከእርሱ ጋር ከተባበርን ትንሣኤውን በሚመስል ትንሣኤ

ደግሞ ከእርሱ ጋር እንተባበራለን።" (ሮሜ 6፥5) "በጥምቀት ከእርሱ ጋር ተቀበራችሁ፤ በጥምቀት ደግሞ ከሙታን ባስነሣው በእግዚአብሔር አሠራር በማመናችሁ ከእርሱ ጋር ተነሣችሁ።" (ቆላ. 2፥12)

9.2 ሞት በአንተ ላይ ምንም ኃይልና ሥልጣን የለውም። "ሞት ሆይ መውጊያህ የት አለ? ሲኦል ሆይ ድል መንሣትህ የት አለ? የሞት መውጊያ ኃጢአት ነው። የኃጢአትም ኃይል ሕግ ነው፤ ነገር ግን በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ድል መንሣትን ለሚሰጠን ለእግዚአብሔር ምሥጋና ይሁን።" (1ቆሮ. 15፥55–57)

9.3 ለሥጋ ፊቃድና ለኃጢአት ሞተሃል። ክርስቶስ በትንሣኤ ኃይል የሞትን ጣር አጥፍቶታል። የሥጋ ሞት ወደ ቤቱ የሚሄድበት የመሸጋገሪያ ድልድይ ብቻ ነው። ከመንፈሳዊ ሞት ነጻ ለወጣ ሰው፣ ሥጋዊ ሞት የሚበሰብሰውን ጥሎ የማይበሰብሰውን የክብር ገላ የመልበሻ መንገድ ነው። "ሞታችኋልና ሕይወታችሁም በእግዚአብሔር ከክርስቶስ ጋር ተሰውሮአልና።" (ቆላ. 3፥3) "እንዲሁም እናንተ ደግሞ ለኃጢአት እንደ ሞታችሁ፤ ግን በክርስቶስ ኢየሱስ በጌታችን ሆናችሁ ለእግዚአብሔር ሕያዋን እንደ ሆናችሁ ራሳችሁን ቁጠሩ።" (ሮሜ 6፥11) እንግዲህ ሞት በክርስቲያኖች ላይ ምንም ኃይል ምንም ሥልጣን የለውም።

## 10. የመዳንን ልብስ አልብሶሃል

"ጽድቅን ለበስሁ እርሱዋም ለበሰችኝ ፍርዱም እንደ መጎናጸፊያና እንደ ኩፋር ነበረ።" (ኢዮብ 29፥14)

"ካህናቶችዋንም ደህንነት አለብሳቸዋለሁ ቅዱሳኖችዋም እጅግ ደስ ይላቸዋል።" (መዝ. 131፥16)

"ጽዮን ሆይ ተነሺ፤ ተነሺ፣ ኃይልንም ልበሺ ቅድስቲቱ ከተማ ኢየሩሳሌም ሆይ ያልተገረዘና ርኩስ ከእንግዲህ ወዲህ አይገባብሽምና ጌጠኛ ልብስሽን ልበሺ።" (ኢሳ. 52፥1)

"እርሱም መልሶ በፊቱ የሚቆሙትን እድፋሙን ልብስ ከእርሱ ላይ አውልቁ አላቸው። እርሱንም እነሆ አበሳህን ከአንተ አርቄአለሁ ጥሩ ልብስም አለብስሃለሁ አለው።" (ዘካ. 3፡4)

"አክሊልን እንደ ለበሰ ሙሽራ በጌጥ ሽልማቷም እንዳጌጠች ሙሽራ የማዳንን ልብስ አልብሶኛልና፤ የጽድቅንም መጎናጸፊያ ደርቦልኛልና በእግዚአብሔር እጅግ ደስ ይለኛል፤ ነፍሴም ሐሴት ታደርጋለች።" (ኢሳ. 61፡10)

የጠፋው ልጅ ታሪክም ሰው ወደ ጌታ በንስሐ ሲመለስ እግዚአብሔር የደህንነት ጸጋ በክርስቶስ እንደሚያለብሰው በምሳሌ ያስተምራል። "አባቱ ግን ባሪያዎቹን አለ፤ ፈጥናችሁ ከሁሉ የተሻለ ልብስ አምጡና አልብሱት፤ ለእጁ ቀለበት ለእግሩም ጫማ ስጡ።" (ሉቃ. 15፡22)

## የውይይት መነሻ ጥያቄዎች

1. ካህናት በጌታ ፊት ለመቆም ጌጠኛና የክብር ልብስ ለበሱ። ይህ ለመንፈሳዊ ሕይወታችን ምን ትርጉም ይሰጠናል?

◆ ____
◆ ____
◆ ____
◆ ____
◆ ____

2. እግዚአብሔር ከሚያለብሰን ነገሮች ውስጥ ጥቂቶቹን ጥቀስ?

◆ ____
◆ ____
◆ ____
◆ ____
◆ ____

3. ጌታ ያለበሰንን በንጽሕና ጠብቀን ለመኖር ምን ይጠበቅብናል?

◆ ____
◆ ____
◆ ____
◆ ____
◆ ____

## 11. ክርስቶስን ለብሰሃል

"ነገር ግን ጌታን ኢየሱስ ክርስቶስን ልበሱት ምኞቱንም እንዲፈጽም ለሥጋ አታስቡ።" (ሮሜ 13፡14)

"በእምነት በኩል ሁላችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጆች ናችሁና ከክርስቶስ ጋር አንድ ትሆኑ ዘንድ የተጠመቃችሁ ሁሉ ክርስቶስን ለብሳችኋል።" (ገላ. 3፡26-27)

__የውይይት መነሻ ጥያቄዎች__

1. ክርስቶስን መልበስ ማለት ምን ማለት ነው?

- 
- 
- 
- 
- 

2. ክርስቶስን የለበሰ ሰው እንዴት ይታወቃል?

- 
- 
- 
- 
- 

3. በቆላስያስ 3:14 የተገለጡትና ልንለብሳቸው የሚገቡን ነገሮች ምንድን ናቸው?

- 
- 
- 
- 
- 

## 12. ሕይወትህ በክርስቶስ ውስጥ ተሰውሮአል

"ሞታችኋልና፤ ሕይወታችሁም በእግዚአብሔር ከክርስቶስ ጋር ተሰውሮአልና፤ ሕይወታችሁ የሆነ ክርስቶስ በሚገለጥበት ጊዜ በዚያን ጊዜ እናንተ ደግሞ ከእርሱ ጋር በክብር ትገለጣላችሁ።" (ቆላ. 3፡3)

"በእኔ ኑሩ እኔም በእናንተ። ቅርንጫፍ በወይኑ ግንድ ባይኖር ከራሱ ሊያፈራ እንዳይቻለው፤ እንዲሁ እናንተ ደግሞ በእኔ ባትኖሩ አትችሉም። እኔ የወይን ግንድ ነኝ እናንተም ቅርንጫፎች ናችሁ። ያለ እኔ ምንም ልታደርጉ አትችሉምና በእኔ የሚኖር እኔም በእርሱ፤ እርሱ ብዙ ፍሬ ያፈራል።" (ዮሐ. 15፡4–5)

"ለቅዱሳኑ ተገልጦአል ለእነርሱም እግዚአብሔር በአሕዛብ ዘንድ ያለው የዚህ ምሥጢር ክብር ባለጠግነት ምን እንደሆነ ሊያስታውቅ ወደደ፤ ምሥጢሩም የክብር ተስፋ ያለው ክርስቶስ በእናንተ ዘንድ መሆኑ ነው።" (ቆላ. 1፡27)

## የውይይት መነሻ ጥያቄዎች

1. በክርስቶስ ውስጥ የመሰወር ምስጢር ምንድነው?

- ______
- ______
- ______
- ______
- ______

2. በእርሱ ውስጥ የመሰወሩ ውጤት ምንድነው?

- ______
- ______
- ______
- ______
- ______

# 13. ወደ ክርስቶስ አካል ተጠምቀሃል

"አይሁድ ብንሆን፤ የግሪክ ሰዎችም ብንሆን፤ ጨዋዎችም ብንሆን እኛ ሁላችን በአንድ መንፈስ አንድ አካል እንድንሆን ተጠምቀናል። ሁላችንም አንድን መንፈስ ጠጥተናል።" (1ቆሮ. 12፡13)

## 14. እግዚአብሔር መርጦሃል

"ዓለም ሳይፈጠር በፊቱ ቅዱሳንና ነውር የሌለን በፍቅር እንሆን ዘንድ በክርስቶስ መረጠን።" (ኤፌ. 1፡4)

የእግዚአብሔር ምርጫ የአድልዎ አይደለም። እግዚአብሔር ልብን የሚያውቅና መንፈስን የሚመዝን ስለሆነ የፍቅሩን ጥሪ የሚቀበሉትን ስለሚያውቃቸው ለራሱ ይለያቸዋል። ይህ የጌታ የመሆንህ ጉዳይ እንዲሁ በድንገት የሆነ ነገር ሳይሆን ከመፈጠርህ በፊት የተወሰነ ጉዳይ ነው። ይህም ማለት ዓለምና በዓለም ያለው ሁሉ ሳይኖር እግዚአብሔር ልብህን አይቶ በፍቅሩ ለራሱ ለየህ ወይም መረጠህ።

"ዓለም ሳይፈጠር በፊቱ ቅዱሳንና ነውር የሌለን በፍቅር እንሆን ዘንድ በክርስቶስ መረጠን።" (ኤፌ. 1፡4) ከዚህ የተሻለ ምንም ምርጫ የለም። ይህ ምርጫ ለሕይወትም ለአገልግሎትም ነው። ንጉሡ ሕዝቅያስ ይህን ስለተረዳ ለካህናት እንዲህ አላቸው፦ "ልጆቼ ሆይ፦ በፊቱ ትቆሙና ታገለግሉት ዘንድ፤ አገልጋዮችም ትሆኑ ዘንድ፤ ታጥኑለትም ዘንድ እግዚአብሔር መርጦአችኋልና ቸል አትበሉ።" (2ኛ ዜና 29፡11) ሐዋርያው ጴጥሮስም ይህ እውነት ከሆነ በፍሬ መገለጽ ስለ አለበት እንዲህ ብሎ ክርስቲያኖችን ይመክራል፦ "ስለዚህ ወንድሞች ሆይ መጠራታችሁንና መመረጣችሁን ታጸኑ ዘንድ ከፊት ይልቅ ትጉ፤ እነዚህን ብታደርጉ ከቶ አትሰናከሉምና። እንዲሁ ወደ ዘላለሙ ወደ ጌታችንና መድኃኒታችን ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ መንግሥት መግባት በሙላት ይሰጣችኋልና።" (2ጴጥ. 1፡10-11)

### <u>የውይይት መነሻ ጥያቄዎች</u>

1. እግዚአብሔር ሰውን የሚመርጠው ለምን ይመስልሃል?

♦ ______________________________

♦ ______________________________

♦ ______________________________

♦ ______________________________

♦ ______________________________

2. የጌታ ምርጫ በሙላት ይፈጸም ዘንድ ከእኛ ምን ይጠበቃል?

♦

- 
- 
- 
- 

## 15. የእግዚአብሔር ቤተሰብ ሆነሃል

"እንግዲያስ ከእንግዲህ ወዲህ ከቅዱሳን ጋር ባላገሮችና የእግዚአብሔር ቤተ ሰዎች ናችሁ እንጂ እንግዶችና መጻተኞች አይደላችሁም። በሐዋርያትና በነቢያት መሠረት ላይ ታንጻችኋል፤ የማዕዘኑም ራስ ድንጋይ ክርስቶስ ኢየሱስ ነው፤ በእርሱም ሕንፃ ሁሉ እየተጋጠመ በጌታ ቅዱስ ቤተ መቅደስ እንዲሆን ያድጋል፤ በእርሱም እናንተ ደግሞ ለእግዚአብሔር መኖሪያ ለመሆን በመንፈስ አብራችሁ ትሠራላችሁ።" (ኤፌ. 2፥19–22)

"እናንተ ግን ከጨለማ ወደሚደነቅ ብርሃኑ የጠራችሁን የእርሱን በጎነት እንድትነግሩ የተመረጠ ትውልድ፤ የንጉሥ ካህናት፤ ቅዱስ ሕዝብ፤ ለርስቱ የተለየ ወገን ናችሁ። እናንተ ቀድሞ ወገን አልነበራችሁም አሁን ግን የእግዚአብሔር ወገን ናችሁ እናንተ ምሕረት ያገኛችሁ አልነበራችሁም። አሁን ግን ምሕረትን አግኝታችኋል።" (1ጴጥ. 2፥9–10)

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከአንድ አባትና እናት ተወልደው በፍቅር ተሳስረው እየተረዳዱና እየተዋደዱ የሚኖሩ ሁሉ ቤተሰብ ይባላሉ። ዋና መታወቂያቸው የአባታቸው ስም ነው። አብዛኛውን ጊዜ የሚኖሩትም አብረው ነው። ከአንድ ቤተሰብ ስለ ተወለዱ በመልክና በጠባይም ይመሳሰላሉ። ለቤተሰብ ስምና ክብር ይኖራሉ። በአዲስ ኪዳንም ውስጥ አንድ ሰው በጌታ ባመነ ጊዜ ወደ ክርስቶስ አካል ውስጥ ስለሚዋሃድ ከእግዚአብሔር ቤተሰብ አባል እንደ አንዱ ይሆናል። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በጌታ ውስጥ ካሉት ሕብረተሰብ ሁሉ ጋር ወንድሞችና እህቶች እንሆናለን። የእግዚአብሔር ቤተሰብ ስለሆንና እግዚአብሔር አባታችን ጌታ ኢየሱስም ወንድማችን፤ መንፈስ ቅዱስ የኅብረታችንና የአንድነታችን መሠረት ስለሚሆን በዘር፤ በጾታ፤ በቋንቋ፤ በቀለምና በመሳሰሉት መለየት ቀርቶ በፍቅር እንተሳሰባለን። መታወቂያችን እግዚአብሔር አባታችን ስለሚሆን ለእርሱ ክብርና ስም እንኖራለን። ዋናው መታወቂያ አርማችን የእግዚአብሔር ፍቅር

ይሆናል። “አብ እንደ ወደደኝ እኔ ደግሞ ወደድኋችሁ፤ በፍቅሬ ኑሩ። ...እኔ እንደ ወደድኋችሁ እርስ በእርሳችሁ ትዋደዱ ዘንድ ትዕዛዜ ይህች ናት።” (ዮሐ. 15፡9፤12) “እርስ በእርሳችሁ ፍቅር ቢኖራችሁ፤ ደቀመዛሙርቴ እንደሆናችሁ ሰዎች ሁሉ በዚያ ያውቃሉ።” (ዮሐ. 13፡35)

ስለዚህ በጌታ ውስጥ ያሉ ሁሉ ዘላለማዊ አባት ብቻ ሳይሆን በቁጥር የማይተመኑ ወንድሞችና እህቶችም አሉአቸው። ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔር ሕዝብ አንድነት ናት። በቤተ ክርስቲያን አማካይነት የእግዚአብሔር ቤተሰብ አብሮ ያድጋል። ሕይወትና በረከት ለቤተሰቡ የሚፈሰው በዚህ ዓይነት አንድነት ውስጥ እንደሆነ ቃሉ ሲመክር እንዲህ ይላል፡- “በጽዮን ተራሮች እንደሚወርድ እንደ አርሞንኤም ጠል ነው። በዚያ እግዚአብሔር በረከቱን ሕይወትንም እስከ ዘላለም አዝዞአልና።” (መዝ. 132፡3) አንተም የዚህ ሕይወትና በረከት ተካፋይ ብቻ ሳትሆን የበረከት ማስተላለፊያ ቧንቧ ነህና የቅዱሳንን ሕብረት ቸል አትበል። “በአንዳንዶችም ዘንድ ልማድ እንደሆነው መሰብሰባችንን አንተው እርስ በእርሳችን እንመካከር እንጂ ይልቁኑ ቀኑ ሲቀርብ እያያችሁ አብልጣችሁ ይህን አድርጉ።” (ዕብ. 10፡25)

## <u>የውይይት መነሻ ጥያቄዎች</u>

1. ቤተሰብ ለሌሎች ያለው ኃላፊነት ምንድነው?

- ______
- ______
- ______
- ______
- ______

2. በቤተሰብ ውስጥ ኅብረትን ወይም አንድነትን ጠብቆ መኖር አስፈላጊ የሆነው ለምንድነው?

- ______
- ______
- ______
- ______
- ______

# 16. የሚማልድልህ ሊቀ ካህን አግኝተሃል

"እንግዲህ በሰማያት ያለ ትልቅ ሊቀ ካህናት ስላለን፤ ጸንተን ኃይማኖታችንን እንጠብቅ።" (ዕብ. 4፡14)

"ስለ እነርሱም ሊያማልድ ዘወትር በሕይወት ይኖራልና ስለዚህ ደግሞ በእርሱ ወደ እግዚአብሔር የሚመጡትን ፈጽሞ ሊያድናቸው ይችላል።" (ዕብ. 7፡25)

በብሉይ ኪዳን ውስጥ ካህናት ሆነው ሲያገለግሉ የቆዩ ነበሩ። አገልግሎታቸው ስለ ሰዎች መማለድና በእግዚአብሔር ፊት መቆም ሰዎችን ወደ አምልኮ ማቅረብ ነበር። ዛሬ ግን ክርስቶስ ኢየሱስ የክርስቲያኖች ሁሉ ሊቀ ካህን ሆኖ በአብ ፊት ቆሞልናል። (ዕብ. 4፡16 ተመልከት) በሁሉ ተፈትኖ ፈተናን ስለ አሸነፈ የእኛ ድካም ይገባዋል፤ ይራራል፤ ይረዳናል። በሚመጣበት ጊዜ እርሱ ጠበቃ ሆኖ ስለእኛ ይቆማል። "ልጆች ሆይ ኃጢአትን እንዳታደርጉ ይህን እጽፍላችኋለሁ። ማንም ኃጢአትን ቢያደርግ ከአብ ዘንድ ጠበቃ አለን።" (1ዮሐ. 2፡2) በራሱ ደም የኃጢአታችንን ሥርየት ያስገኘልን ስለ እኛ ሊቀ ካህንም ጠበቃም ሆኖ ስለቆመልን ወደ አብ ማለትም ወደ ቅድስተ ቅዱሳን የመግባት ድፍረት ተሰጥቶናል። እርሱ አይሰለችም፤ አይደክምም ቀንና ሌሊት አማላጅህ ሆኖ በእግዚአብሔር ፊት አለልህ።

## <u>የውይይት መነሻ ጥያቄዎች</u>

1. ሊቀ ካህን ለምን አስፈለገ?

◆ ______
◆ ______
◆ ______
◆ ______
◆ ______

2. የሊቀ ካህን አገልግሎት ምንድነው?

◆ ______
◆ ______
◆ ______

- ____________________
- ____________________

3. ሊቀ ካህናችን ክርስቶስ ኢየሱስ ከሌሎች ሊቀ ካህናት የሚለየው በምንድነው?

- ____________________
- ____________________
- ____________________
- ____________________
- ____________________

## 17. አጽናኝ አለህ

"ብትወዱኝ ትዕዛዜን ጠብቁ። እኔም አብን እለምናለሁ ለዘላለም ከእናንተ ጋር እንዲኖር ሌላ አጽናኝ ይሰጣችኋል እርሱም ዓለም የማያየውና የማያውቀው ስለ ሆነ ሊቀበለው የማይቻለው የእውነት መንፈስ ነው ነገር ግን ከእናንተ ዘንድ ስለሚኖር በውስጣችሁም ስለሚሆን እናንተ ታውቃላችሁ።" (ዮሐ.14፡15–17)

ይህንን ቃል ኪዳን ለመፈጸም እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስን በበዓለ ኀምሳ ቀን ልኮአል። "በበዓለ ኀምሳ የተባለውም ቀን በደረሰ ጊዜ፤ ሁሉም በአንድ ልብ ሆነው አብረው ሳሉ፤ በሁሉም መንፈስ ቅዱስ ሞላባቸው፤ መንፈስም ይናገሩ ዘንድ እደሰጠቻው በሌላ ልሳኖች ይናገሩ ጀመር።" (ሐዋ. 2፡1፤4) ስለ ኃጢአት ወቅሶን ለንስሐ ያበቃን መንፈስ ቅዱስ ነው። በአመንንም ጊዜ ለቤዛ ቀን ያተመን እርሱ ነው። ሙላትን ከተቀበልን ኃይልን ብቻ ሳይሆን የጸጋንም ስጦታ የሚሰጠን ለአገልግሎትም የሚቀባን እርሱ ነው። የማይለየን አጽናኝ ስለሆነ ሁል ጊዜ ከእኛ ጋር አለ። ወደ እውነት ሁሉ ይመራናል። የቃሉን መገለጥ ይሰጠናል። በድካማችን፤ በሃዘናችንም ከእኛ የማይለይ እውነተኛ ታማኝ አጽናኝ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ብቻ ነው። እንደ መንፈስ ቅዱስ ያለውን አጽናኝ ማግኘት፤ እንዴት መታደል ነው።

## የውይይት መነሻ ጥያቄዎች

1. አጽናኝ ማለት ምን ማለት ነው?

- 
- 
- 
- 
- 

2. ይህ ስም ለምን ለመንፈስ ቅዱስ ተሰጠ?

- 
- 
- 
- 
- 

3. አጽናኛችን መንፈስ ቅዱስ በሕይወታችን የሚሠራውን ሥራዎች ዘርዝር።

- 
- 
- 
- 
- 

4. የእኛ ኃላፊነት ምንድነው?

- 
- 
- 
- 
- 

## 18. በክርስቶስ የክብሩ ወራሽ ሆነሃል

"ስለዚህም የፊተኛው ኪዳን ሲጸና ሕግን የተላለፉትን የሚቤዥ ሞት ስለ ሆነ፥ የተጠሩት የዘላለምን ርስት የተስፋ ቃል እንዲቀበሉ እርሱ የአዲስ ኪዳን መካከለኛ ነው።" (ዕብ. 9፡15)

"አሁንም ለእግዚአብሔር ያንጻችሁ ዘንድ በቅዱሳንም ሁሉ መካከል ርስትን ይሰጣችሁ ዘንድ ለሚችል ለጸጋው ቃል አደራ ሰጥቻችኋለሁ።" (ሐዋ. 20፡32)

"…ለማያልፍም ርስት እንደ ምሕረቱ ብዛት ሁለተኛ የወለደን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና አባት ይባረክ።" (1ጴጥ. 1፡4)

"ንጉሡም በቀኙ ያሉትን እንዲህ ይላቸዋል፦ እናንተ የአባቴ ብሩካን ኑ ዓለም ከተፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ የተዘጋጀላችሁን መንግሥት ውረሱ።" (ማቴ. 25፡34)

ይህን ውርስ ሥጋና ደም መቀበል አይችልም። "ወንድሞች ሆይ ይህን እላለሁ፦ ሥጋና ደም የእግዚአብሔርን መንግሥት ሊወርሱ አይችሉም፤ የሚበሰብሰውም የማይበሰብሰውን አይወርስም።" (1ቆሮ. 15፡50) የከበረው የትንሣኤ አካል ከለበስን በኋላ የምንቀበለው የዘላለም ርስታችንን ነው። ስለዚህ ርስት ባለ ጠግነት በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ብዙ ጊዜ ተጠቅሷል። ለምሳሌ ያህል ብንጠቅስ፦

18.1 ሐዋርያው ጳውሎስ መንፈሳዊ ዓይኖቻችን ተከፍተው የዚህን ውርስ ባለ ጠግነት እንድናይ ሲጸልይ "ይህም የልባችሁ ዓይኖች ሲበሩ የመጥራቱ ተስፋ ምን እንዲሆን በቅዱሳንም ዘንድ ያለውን የርስት ክብር ባለ ጠግነት ምን እንዲሆን ለምናምንም ከሁሉ የሚበልጥ የኃይሉ ታላቅነት ምን እንደሆነ ታውቁ ዘንድ ነው፤" (ኤፌ. 1፡18) ይላል።

18.2 ስለ ውርስ እርግጠኝነት ሲናገር እንዲህ ይላል "እርሱም የርስታችን መያዣ ነው፦ ለእግዚአብሔር ያለውን ሁሉ እስኪዋጅ ድረስ፣ ይህም ለክብሩ ምሥጋና ይሆናል።" (ኤፌ. 1፡14)

18.3 ስለዚህ ውርስ እግዚአብሔርን ሲያመሰግን እንዲህ ይላል "በእግዚአብሔር እውቀት እያደጋችሁ፤ ከደስታም ጋር በሁሉ ለመጽናናት፤ ለመታገስ እንደ ክብሩ ጉልበት መጠን በኃይል ሁሉ እየበረታችሁ፤ በቅዱሳንም ርስት ብርሃን እንድንካፈል ያበቃንን አብን እያመሰገናችሁ በነገር ሁሉ ደስ ልታሰኙ ለጌታ እንደሚገባ ትመላለሱ ዘንድ እንለምናለን።" (ቆላ. 1፡12)

## የውይይት መነሻ ጥያቄዎች

1. በእግዚአብሔር ውስጥ ያለንን ውርስ ዘርዝር።

- ______
- ______
- ______
- ______
- ______

2. መንግሥተ ሰማይን በመውረስና ክብሩን በመውረስ መካከል ልዩነት ያለ ይመስልሃልን?

- ______
- ______
- ______
- ______
- ______

3. አዎን ካልክ ልዩነቱን ዘርዝር?

- ______
- ______
- ______
- ______

## 19. እግዚአብሔር ወዶሃል

"በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና።" (ዮሐ. 3፡16)

"የእግዚአብሔር ልጆች ተብለን ልንጠራ አብ እንዴት ያለውን ፍቅር እንደ ሰጠን እዩ፥ እንዲሁም ነን። ስለዚህ ምክንያት ዓለም እርሱን ስላላወቀው እኛን አያውቀንም።" (1ዮሐ. 3፡1)

"እርሱ ስለ እኛ ነፍሱን አሳልፎ ሰጥቶአልና በዚህ ፍቅርን አውቀናል እኛም ስለ ወንድሞቻችን ነፍሳችንን አሳልፈን እንድንሰጥ ይገባናል።" (1ዮሐ. 3፡16)

"የእናንተ ሥርና መሠረት በፍቅር ይጸና ዘንድ ከቅዱሳን ሁሉ ጋር ስፋቱና ርዝመቱ፤ ከፍታው ጥልቀቱም ምን ያህል መሆኑን ለማስተዋል፤

ከመታወቅም የሚያልፈውን የክርስቶስን ፍቅር ለማወቅ ትበረቱ ዘንድ እስከ እግዚአብሔር ፍጹም መላት ደርሳችሁ ትሞሉ ዘንድ" (ኤፌ. 3፡18–19)

## የውይይት መነሻ ጥያቄዎች

1. ፍቅር ምንድነው?

♦ ____________________

♦ ____________________

♦ ____________________

♦ ____________________

♦ ____________________

2. የእግዚአብሔር ፍቅር በምን ይለካል?

♦ ____________________

♦ ____________________

♦ ____________________

♦ ____________________

♦ ____________________

3. የእግዚአብሔርን ፍቅር መቀበል በሕይወታችን ውስጥ ምን ያስገኛል?

♦ ____________________

♦ ____________________

♦ ____________________

♦ ____________________

♦ ____________________

# 20. ከመለኮታዊ ባሕርይ ተካፋይ ሆነሃል።

"የመለኮት ኃይል፥ በገዛ ክብሩና በበጎነቱ የጠራንን በማወቅ ለሕይወትና እግዚአብሔርን ለመምሰል የሚሆነውን ነገር ሁሉ ስለ ሰጠን በእግዚአብሔርና በጌታችን በኢየሱስ ዕውቀት ጸጋና ሰላም ይብዛላችሁ። ስለ ክፉ ምኞት በዓለም ካለው ጥፋት አምልጣችሁ ከመለኮት ባሕርይ ተካፋዮች በተስፋ ቃል እንድትሆኑ፥ በእነዚያ ክብርና በጎነት የተከበረና እጅግ ታላቅ የሆነ ተስፋን ሰጠን።" /2ጴጥ. 1፡3–4/

ይህ በመንፈስ ቅዱስ የተሰጠን ታላቅና አስደናቂ የእግዚአብሔር በረከት ነው። ይህ የሆነው የተትረፈረፈ ሕይወት እንድንኖር፤ እግዚአብሔርን እንድንመስልና ከዓለምም ኃጢያት እንድናመልጥ ነው። ይህም እንዲሆን

እግዚአብሔር ከሥጋ ያልሆነ መለኮታዊ ኃይሉን ሰጥቶናል። ስለዚህ ይህ መለኮታዊ ኃይል ተካፋይ የሆነ የእግዚአብሔር ልጅ ኃጢያትን ለመሥራት ማመካኘት አይችልም።

## <u>የውይይት መነሻ ጥያቄዎች</u>

1. ከመለኮታዊ ባሕርይ ተካፋይ መሆን ማለት አምላክ መሆን ማለት ነውን?

- 
- 
- 
- 
- 

2. ታዲያ ምን ማለት ነው?

- 
- 
- 
- 
- 

3. ከመለኮታዊ ባሕርይ ተካፋይ መሆን በሕይወታችን ውስጥ ምን ለውጥ ያስከትላል?

- 
- 
- 
- 
- 

## 21. ከጨለማ ወደሚደነቅ ብርሃን አምጥቶሃል

"እናንተ ግን ከጨለማ ወደሚደነቅ ብርሃን የጠራችሁን የእርሱን በጎነት እንድትነግሩ የተመረጠ ትውልድ፤ የንጉሥ ካህናት፤ ቅዱስ ሕዝብ፤ ለርስቱ የተለየ ወገን ናችሁ።" (1ጴጥ. 2፡9)

"የዛብሎን ምድርና የንፍታሌም ምድር፤ የባሕር መንገድ፤ በዮርዳኖስ ማዶ የአሕዛብ ገሊላ፤ በጨለማ የተቀመጠው ሕዝብ ታላቅ

ብርሃን አየ፤ በሞት አገርና ጥላ ለተቀመጡትም ብርሃን ወጣላቸው።" (ማቴ. 4፡16)

የእግዚአብሔር ቃል ከዚህ አስደናቂ የክብር ብርሃን ጋር በማያያዝ ስለ ሕይወታችን የሚከተለውን ይመሰክራል፦

21.1 "በክርስቶስ ፊት የእግዚአብሔርን የክብሩን እውቀት ብርሃን እንዲሰጥ በልባችን ውስጥ የበራ፦ በጨለማ ብርሃን ይብራ ያለ እግዚአብሔር ነውና።" (2ቆሮ. 4፡6)

21.2 "ደግሞም ኢየሱስ፦ እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ የሚከተለኝም የሕይወት ብርሃን ይሆንለታል እንጂ በጨለማ አይመላለስም ብሎ ተናገራቸው።" (ዮሐ. 8፡12)

21.3 "እናንተ የዓለም ብርሃን ናችሁ። በተራራ ላይ ያለች ከተማ ልትሰወር አይቻላትም።" (ማቴ. 5፡14)

21.4 "ቀድሞ ጨለማ ነበራችሁና አሁን ግን በጌታ ብርሃን ናችሁ። የብርሃኑ ፍሬ በበጎነትና በጽድቅ በእውነትም ሁሉ ነውና ለጌታ ደስ የሚያሰኘውን እየመረመራችሁ እንደ ብርሃን ልጆች ተመላለሱ፤ ፍሬም ከሌለው ከጨለማ ሥራ ጋር አትተባበሩ፤" (ኤፌ. 5፡8)

እንግዲህ የእግዚአብሔር ልጆች በብርሃን ውስጥ የምንኖር ብቻ ሳንሆን በጨለማ ውስጥ ላሉት ደግሞ የክብሩን ብርሃን የምናበራ ብርሃን ነን። «የሕይወት ቃል እያቀረባችሁ በዓለም እንደ ብርሃን ትታያላችሁ፤» (ፊል. 2፡15) «መልካሙን ሥራችሁን አይተው በሰማያት ያለውን አባታችሁን እንዲያከብሩ ብርሃናችሁ እንዲሁ በሰው ፊት ይብራ።» (ማቴ. 5፡16)

## የውይይት መነሻ ጥያቄዎች

1. የክርስቶስ መንግሥት ለምን የብርሃን መንግሥት ይባላል?

♦ ______________________

♦ ______________________

- 
- 
- 

2. የሚደነቅ ብርሃን ለምን ተባለ?

- 
- 
- 
- 
- 

3. ብርሃን በመሆንና በብርሃን ውስጥ በመኖር መካከል ልዩነቱ ምንድነው?

- 
- 
- 
- 
- 

## 22. ምሕረቱን ተቀብለሃል

የእግዚአብሔር ምህረት ስንል ምን ማለታችን ነው? ምህረት ለምን ያስፈልጋል? እግዚአብሔር የምህረትን ጩኸት እንዴት ነው የሚያደምጠው? (ማር. 10:46-52)

"እግዚአብሔርን አመስግኑ ቸር ነውና፤ ምሕረቱ ለዘላለም ነውና። ቸር እንደ ሆነ ምሕረቱም ለዘላለም እንደሆነች የእስራኤል ቤት አሁን ይንገሩ። ቸር እንደ ሆነ ምሕረቱም ለዘላለም እንደሆነች የአሮን ቤት አሁን ይንገሩ። ቸር እንደ ሆነ ምሕረቱ ለዘላለም እንደ ሆነች እግዚአብሔርን የሚፈሩ ሁሉ አሁን ይንገሩ።" (መዝ. 117፡1-4)

እግዚአብሔር ስላለው ምሕረት ብዙ ነገር ተዘርዝሮአል። ከእነዚህ ውስጥ ጥቂቱን ለመጥቀስ ያህል:-

22.1 ምሕረቱ በየቀኑ አዲስ ነው። "ያልጠፋነው ከእግዚአብሔር ምሕረት የተነሣ ነው፤ ርኅራኄው አያልቅምና። ማለዳ ማለዳ አዲስ ነው፤ ታማኝነቱም ብዙ ነው።" (ሰቆ.ኤር. 3፡22-23)

22.2 ምሕረቱ ዘላለማዊ ነው። "ቸር ነውና፤ ምሕረቱ ለዘላለም ነውና እግዚአብሔርን አመስግኑት።" (መዝ. 106፥1)

## የውይይት መነሻ ጥያቄዎች

1. ምህረት ምንድነው?

◆ ___
◆ ___
◆ ___
◆ ___
◆ ___

2. ለምንድነው ምህረትን ያገኘነው?

◆ ___
◆ ___
◆ ___
◆ ___
◆ ___

3. "ምህረቱ በየቀኑ አዲስ ነው" ስንል ምን ማለታችን ነው?

◆ ___
◆ ___
◆ ___
◆ ___
◆ ___

# 23. በመንፈሳዊ በረከቶች ሁሉ ባርኮሃል

"በክርስቶስ በሰማያዊ ሥፍራ በመንፈሳዊ በረከት ሁሉ የባረከን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና አባት ይባረክ።" (ኤፌ. 1፥3)

## የውይይት መነሻ ጥያቄዎች

መንፈሳዊ በረከቶች ምንና ምንን ያካትታሉ?

◆ ___
◆ ___
◆ ___
◆ ___

ጌታ ኢየሱስ የኃጢአትን ዕዳ ስለ ከፈለ ለመንፈሳዊ በረከት ዕንቅፋት የሚሆኑ ነገሮች ሁሉ ከመንገድ ላይ ተወግደዋል። እነዚህ መንፈሳዊ በረከቶች ሁለት ክፍሎች አላቸው። የመጀመሪያው መንፈሳዊ በረከት፦ መሆን የሚገባንን ያደርገናል፤ እያደረግንም ያለው የእግዚአብሔር ጸጋ ነው። ይህ የእግዚአብሔር ከመሆን ጀምሮ እግዚአብሔር ለልጆቹ የሰጠውና ገና ሊሰጣቸው ያዘጋጃቸውን በረከቶች ሁሉ ያጠቃልላል። እነዚህ ሁሉ በመስቀሉ ሥራ ምክንያት የተፈጸሙ በረከቶች ናቸው። በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ቀደም ብለን የጠቀስናቸውና ገና የምንጠቅሳቸውን፣ ዛሬ በዚህ ውስጥ በአእምሮ ለመረዳት የማንችላቸውን ሁሉ ይጨምራል። ከበረከት ሁሉ በላይ የሆነ በረከት ግን በክርስቶስ ደም ነጽቶ የእግዚአብሔር ልጅ መሆን ነው።

ሌላው ዓይነት በረከት እላይ በጠቀስናቸው በረከቶች ምክንያት እግዚአብሔር ለክብሩ በሕይወታችን ሌሎችን ለማገልገል በመንፈስ ቅዱስ የሚሰጠን መንፈሳዊ በረከቶች ናቸው። እነዚህ መንፈስ ቅዱስ ከሚሰጣቸው የጸጋ ስጦታ ጋር የተያያዙ ናቸው። የእግዚአብሔር ልጆችና የክብሩ ወራሾች ከሆንን በኋላ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ የጸጋን ስጦታ ለእያንዳንዱ ሰው እያካፈለ ይሰጠዋል። ስጦታቸውን የማያውቁ ወይም አውቀው እንደሚገባ የማይጠቀሙበት አሉ እንጂ መንፈሳዊ ስጦታ የሌለው ክርስቲያን የለም። እግዚአብሔር በመንፈሳዊ በረከት ከባረከን በኋላ እንደ ሰማያዊ ዜጋዎች እንድንኖር በመንግሥቱ ሥራ ላይ ተሠማርተን ፍሬ የምናፈራባቸውን የጸጋ ስጦታን ይሰጠናል። እግዚአብሔር በስጦታ ስለማይወሰን እንደ መንፈስ ፈቃድ እያስታጠቀ በረከትና ዕድገትን ለሚያመጣ አገልግሎት ያሰልፈናል። አንተም ተባርከሃልና እምነህ ተቀበል። በረከቶችህንም በእምነት በሥራ ላይ አውላቸው። እርሱ ውጤቱን ይባርክልሃል። ከዚህ የተለዩ በረከቶች ምን ምን ናቸው? (“ሰማያዊ በረከትን መውረስ” የሚለውን መጽሐፍ አንብብና ጥያቄውን መልስ)

## የውይይት መነሻ ጥያቄዎች

1. የእግዚአብሔር በረከት ምንና ምንን ያጠቃልላል?

- ____________________
- ____________________

♦
♦
♦

2. በረከትን ለመውረስ ምን ያስፈልጋል?

♦
♦
♦
♦
♦

3. በረከትን ለመጠበቅ እንዴት መኖር አለብን?

♦
♦
♦
♦
♦

## 24. መንፈሳዊ ሥልጣን ተሰጥቶሃል

"እነሆ እባቡንና ጊንጡን ትረግጡ ዘንድ፤ በጠላትም ኃይል ሁሉ ላይ ሥልጣን ሰጥቻችኋለሁ፤ የሚጎዳችሁም ምንም የለም።" (ሉቃ. 10፡19)

ይህ መንፈሳዊ ሥልጣን በሰማይና በምድር ሥልጣን ሁሉ ካለው ከክርስቶስ ኢየሱስ ለልጆቹ ሁሉ የተሰጠ ሥልጣን ነው። "ኢየሱስም ቀረበና እንዲህ ብሎ ተናገራቸው፤ ሥልጣን ሁሉ በሰማይና በምድር ተሰጠኝ።" (ማቴ. 28፡18) መንፈሳዊ ሥልጣንን ከመንፈሳዊ ስጦታዎች ለይቶ መረዳት በጣም አስፈላጊ ነው። መንፈሳዊ ስጦታዎችን መንፈስ ቅዱስ እንደ ፈቃዱ ለአገልግሎቱ ወይም ለጥቅም የሚሰጣቸው ሲሆኑ መንፈሳዊ ሥልጣን ግን ጠላታችንን አሸንፈን በድልና በቅድስና ለመኖር እንድንችል ከክርስቶስ ኢየሱስ በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ለእያንዳንዳችን የተሰጠ ስጦታ ነው። እባቡንና ጊንጡን እንድንረግጥና በሥልጣን እንድንመላለስ ሥልጣን ተሰጥቶናል። "እንግዲህ ለእግዚአብሔር ተገዙ፤ ዲያቢሎስን ግን ተቃወሙት ከእናንተ ይሸሻል፤ ወደ እግዚአብሔር ቅረቡ ወደ እናንተም ይቀርባል።" (ያዕ. 4፡7-8)

**የውይይት መነሻ ጥያቄዎች**

1. መንፈሳዊ ሥልጣን የተሰጠን በምን ላይ ነው?

- 
- 
- 
- 
- 

2. መንፈሳዊ ሥልጣን የሚሰጠው ለምንድነው?

- 
- 
- 
- 
- 

3. በመንፈሳዊ ሥልጣናችን እንደሚገባ ለመጠቀም እንዴት መኖር ይገባናል?

- 
- 
- 
- 
- 

## 25. የእግዚአብሔር ዕቃ ጦር ተሰጥቶሃል

"በቀረውስ በጌታና በኃይሉ ችሎት የበረታችሁ ሁኑ የዲያቢሎስን ሽንገላ ትቃወሙ ዘንድ እንዲቻላችሁ የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ሁሉ ልበሱ።" (ኤፌ. 6፡10–11)

“በሰው ልማድ ምንም እንኳን የምንመላለስ ብንሆን እንደ ሰው ልማድ አንዋጋም የጦር ዕቃችን ሥጋዊ አይደለምና፤ ምሽግን ለመስበር ግን በእግዚአብሔር ፊት ብርቱ ነው።” (2ቆሮ. 10፥3-4)

ይህ የጦር ዕቃ ለእግዚአብሔር ወታደሮች ሁሉ የሚያስፈልግ መንፈሳዊ መሣሪያ ነው። እነዚህ መሣሪያዎች የሚከተለውን ዝርዝር ያካትታሉ፥

25.1 የጌታ ኃይል፡- ይህ ከመሣሪያ ሁሉ የሚቀድም መሆን ይገባዋል።

25.2 የወገብ መታጠቂያ፡- እውነት፤ ክርስቶስና የእግዚአብሔር ቃል ናቸው።

25.3 የጽድቅ ጥሩር፡- ልባችንን የምንሸፍንበት የክርስቶስ ጽድቅ ነው።

25.4 መጫሚያ፡- የክርስቶስ የወንጌል እውነት ነው። ለወንጌል ምስክርነት ዝግጁ መሆንን ያጠቃልላል።

25.5 የመከላከያ ጋሻ፡- ይህ ጠላታችን ሰይጣን የሚወረውረውን ፍላጻ ሁሉ የምንመክትበት በጌታ ላይ የተመሠረተ እምነታችን ነው።

25.6 የራስ ቁር፡- ራሳችንን የምንከላከልበት ጠንካራ ቆብ ነው። ይህ ቆብ ደህንነታችንን ይወክላል። በአእምሮአችን መንፈስ መታደስንም ይጠይቃል።

25.7 የመንፈስ ሰይፍ፡- የመንፈስ ሰይፋችን የእግዚአብሔር ቃል ነው። ይህ ሰይፍ የተሰጠን ለመከላከያ ሳይሆን ጠላታችንን እንድናጠቃበት ነው። የእግዚአብሔር ቃል ሁለት አፍ ካለው ሰይፍ ይበልጥ የተሳለ ነውና። (ዕብ. 4፥12) ተመልከት።

25.8 ጸሎት፡- ጸሎት እላይ የተጠቀሱትን መሣሪያዎች ሁሉ ኃያል የሚያደርግ ታላቅ መሣሪያችን ነው። የጠላትን ምሽግ ሁሉ የሚያፈርስና

ማንም ሊቋቋመው የማይችል ታላቅ መሣሪያ ነው። ይህም በመንፈስ ቅዱስ በመማለድ፣ በመመራትና በመቀባት የምንጸልየው ጸሎት ነው። መጸለይ ብቻ ሳይሆን በመንፈስ መቃተትን ይጠይቃል። "እናንተ ግን ወንድሞች ሆይ ከሁሉ ይልቅ በተቀደሰ ሃይማኖታችሁ ራሳችሁን ለማነጽ እየተጋችሁ በመንፈስ ቅዱስም እየጸለያችሁ፣..." (ይሁዳ 1፥20)

25.9 ትጋት፦ በተሰጠው መሣሪያ ተጠቅሞ ጠላትን አሸንፎ መኖር የሚችል ንቁና ትጉ ወታደር ብቻ ነው። መንፈሳዊ ንቃትና ጽናት ሲኖረን እንተጋለን። ቃሉም "ንቁ በሃይማኖትም ቁሙ፤ ጎልምሱ ጠንክሩ።" (1ቆሮ. 16፥13) ከማለቱም ሌላ "የእውነትን ቃል በቅንነት የሚናገር የማያሳፍርም ሠራተኛ ሆነህ የተፈተነውን ራስህን ለእግዚአብሔር ልታቀርብ ትጋ።" (2ጢሞ. 2፥15) ይላል።

## የውይይት መነሻ ጥያቄዎች

1. የጦር ዕቃ ለምን ያስፈልጋል? ለምንስ ተሰጠን?

- ______________________________
- ______________________________
- ______________________________
- ______________________________
- ______________________________

2. ውጊያችን ከማን ጋር ነው?

- ______________________________
- ______________________________
- ______________________________
- ______________________________
- ______________________________

3. እንዴት ነው የምንዘጋጀው? የመሣሪያውን ዓይነትና አጠቃቀም መረዳት ለምን ይጠቅማል?

- ______________________________
- ______________________________
- ______________________________
- ______________________________
- ______________________________

4. የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር መልበስ ለምን ያስፈልጋል?

♦ ______________________________

♦ ______________________________

♦ ______________________________

## 26. ከክርስቶስ ጋር በሰማያዊ ሥፍራ አስቀምጦሃል

"በክርስቶስ ኢየሱስ ለእኛ ባለው ቸርነት ከሁሉ የሚበልጠውን የጸጋውን ባለጠግነት ያሳይ ዘንድ፤ ከእርሱ ጋር አስነሣን፤" (ኤፌ. 2፥6)

በክርስቶስ ውስጥ ስለሆንክ እግዚአብሔር ከፍ አድርጎና አክብሮ ከልጁ ጋር አስቀምጦሃል። እግዚአብሔር ይህን ካደረገበት ምክንያቶች አንደኛው የፍቅሩን፤ የፀጋውንና የምሕረቱን ጥልቀት ለማሳየት ሲሆን በሁለተኛ ደረጃ ነገሮችን ከሰማያዊ አንጻር እንድናይና በምድራዊ ሳይሆን በሰማያዊ አስተሳሰብ ለእርሱ እንድንኖር ነው። ቃሉም ስለዚህ ሲመሰክር "እኛ አገራችን በሰማይ ነውና፤ ከዚያም ደግሞ የሚመጣ መድኃኒት እርሱንም ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን እንጠባበቃለን።" (ፊል. 3፥20) ይላል። ሌላው ማስታወስ ያለብን ነገር እግዚአብሔር አክብሮ ከፍ ስለ አደረገን ከዚህ ከከበረው የቅድስና ዙፋን ወርደን በኃጢያት ቆሻሻ ላይ መቀመጥ ፈጽሞ እንደማይገባን ነው። አመለካከታችን፤ ራዕያችን፤ ፍላጎታችንና ሩጫችን ሁሉ የተቀመጥንበትን ሰማያዊ ክብር ማንጸባረቅ ይኖርበታል።

### <u>የውይይት መነሻ ጥያቄዎች</u>

1. በሰማያዊ ስፍራ የመቀመጥ ምስጢር ምንድነው?

♦ ______________________________

♦ ______________________________

♦ ______________________________

♦ ______________________________

♦ ______________________________

2. በክርስቶስ ቀኝ መቀመጥ የምን ምልክት ነው?

♦ ______________________________

♦ ______________________________

♦ ______________________________

♦
♦

3. አኗኗርህ ምን ይመስላል?

♦
♦
♦
♦
♦

## 27. ከጨለማ ሥልጣን አድኖሃል

"እርሱ ከጨለማ ሥልጣን አዳነን፤ ቤዛነቱንም እርሱንም የኃጢአትን ስርየት ወደ አገኘንበት ወደ ፍቅሩ ልጅ መንግሥት አፈለሰን።" (ቆላ. 1፥13)

ከጨለማ ሥልጣን መዳናችን ብቻ ሳይሆን ወደ ክርስቶስ የፍቅር መንግሥት አስገብቶናል። ይህም በመሆኑ የምንኖረው በፍቅር መንግሥት ውስጥ ነው። ሐዋርያው ዮሐንስ እንደሚናገረው፤ ይህ የመዳናችን ምልክት ነው። "ወንድሙን የሚወድ በብርሃን ይኖራል ማሰናከያም የለበትም፣ ወንድሙን የሚጠላ ግን በጨለማ አለ፤ በጨለማም ይመላለሳል፤ የሚሄድበትን አያውቅም፣ ጨለማም ዓይኖቹን አሳውሮታልና።" (1ዮሐ. 2፥10–11) በክርስቶስ መንግሥት ውስጥ የሚለበሰውና የእግዚአብሔር ልጆች የመታወቂያ አርማችን ፍቅር ነው። "እርስ በእርሳችሁ ፍቅር ቢኖራችሁ፤ ደቀ መዛሙርቴ እንደሆናችሁ ሰዎች ሁሉ በዚህ ያውቃሉ።" /ዮሐ. 13፥35/

### የውይይት መነሻ ጥያቄዎች

1. የጨለማ ሥልጣን ምንድነው?

♦
♦
♦
♦
♦

2. በምን መንገድ ነው የሚሠራው?

- 
- 
- 
- 
- 

3. የጨለማን ሥልጣን ለማሸነፍ እንዴትና የት መኖር አለብን?

- 
- 
- 
- 
- 

## 28. የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ ሆነሃል

"ወይስ ሥጋችሁ ከእግዚአብሔር የተቀበላችሁት በእናንተ የሚኖረው የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ እንደ ሆነ አታውቁምን? በዋጋ ተገዝታችኋልና ለራሳችሁ አይደላችሁም ስለዚህ በሥጋችሁ እግዚአብሔርን አክብሩ።" (1ቆሮ. 6፥19–20)

"የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ እንደ ሆናችሁ የእግዚአብሔርም መንፈስ እንዲኖርባችሁ አታውቁምን? ማንም የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ ቢያፈርስ እግዚአብሔር እርሱን ያፈርሰዋል፤ የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ቅዱስ ነውና፤ ያውም እናንተ ናችሁ።" (1ቆሮ. 3፥16–17)

ቤተ መቅደስ ለእግዚአብሔር የተለየ፤ የእግዚአብሔር ክብር የሰፈነበት፤ የእግዚአብሔር የሆነ ነገር ብቻ የሚቀመጥበትና እግዚአብሔር የሚመለክበት ቦታ ነው። ጌታ ልባችንንም የራሱ ቤተ መቅደስ ሲያደርገው ለዚህ ዓይነት አገልግሎት ስለሆነ ቃሉ "በሰውም ወደ ተጣለ በእግዚአብሔር ዘንድ ግን ወደ ተመረጠና ክቡሩ ወደ ሆነው ወደ ሕያው ድንጋይ ወደ እርሱ እየቀረባችሁ፤ እናንተ ደግሞ እንደ ሕያዋን ድንጋዮች ሆናችሁ፣ በኢየሱስ ክርስቶስ ለእግዚአብሔር ደስ የሚያሰኝ መንፈሳዊ መስዋዕትን

ታቀርቡ ዘንድ ቅዱሳን ካህናት እንድትሆኑ መንፈሳዊ ቤት ለመሆን ተሠሩ።" (1ጴጥ. 2፥4-5) ይላል። መቀደስ ማለት መለየት ማለት ነው። ስለሆነ ጌታን በልባችን የምንቀድሰው ሌላውን አስወግደን ልባችንን የእርሱ ብቻ በማድረግ ነው። መቅደሱ ስለሆነ ጌታ በእኛ ውስጥ ይኖራል። "የሚወደኝ ቢኖር ቃሌን ይጠብቃል አባቴም ይወደዋል ወደ እርሱም እንመጣለን በእርሱም ዘንድ መኖሪያ እናደርጋለን።" (ዮሐ. 14፥23)

## የውይይት መነሻ ጥያቄዎች

1. ቤተ መቅደስ ምንድነው?

- ____
- ____
- ____
- ____
- ____

2. የመንፈስ ቅዱስ መኖሪያ ከሆንን ሕይወታችንን እንዴት መጠበቅ ይገባናል?

- ____
- ____
- ____
- ____
- ____

3. "...ማንም የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ ቢያፈርስ እግዚአብሔር እርሱን ያፈርሰዋል" ሲል ምን ማለት ነው?

- ____
- ____
- ____
- ____
- ____

## 29. የክርስቶስ ፍቅር በመንፈስ ቅዱስ በልብህ ፈሶአል

"ይህም ብቻ አይደለም፤ ነገር ግን መከራ ትዕግሥትን እንዲያደርግ፤ ትዕግሥትም ፈተናን፤ ፈተናም ተስፋን እንዲያደርግ አያወቅን በመከራችን ደግሞ እንመካለን።" (ሮሜ. 5፡3)

ይህ ፍቅር፤ ክርስቶስ በመስቀል ላይ የገለጸው ዓይነት ፍቅር ነው። በሥጋ የሚፈጠር አይደለም። መንፈስ ቅዱስ ያንን ፍቅር በልባችን ውስጥ አፈሰሰው። ይህ ፍቅር፤ ራስን የመስጠት ወይም የመስዋዕትነት ፍቅር ነው። አይሟሽሽም፤ አይለወጥም፤ አይሰለችም፤ ፍጹምነት ያለው ዘላለማዊ ፍቅር ነው። እግዚአብሔር በዚህ ፍቅር ነው የወደደን፤ ከዚህም የሚበልጥ ፍቅር የለም። ይህ ፍቅር እግዚአብሔርን እንድንወድ ያደርገናል። "እርሱ አስቀድሞ ወዶናልና እኛ እንወደዋለን።" (1ዮሐ. 4፡19) ወንድሞቻችንን እንድንወድድ ያስችለናል። "ኃጢአትን የሚያደርግ ሁሉ ዓመፅን ደግሞ ያደርጋል፤ ኃጢአትም ዓመፅ ነው።" (1ዮሐ. 3፡4) ይህ መለኮታዊ ፍቅር ነው የሚወድዱንን ብቻ ሳይሆን የሚጠሉንንም ለመውደድ የሚያበቃን። "እኔ ግን እላችኋለሁ በሰማያት ላለ አባታችሁ ልጆች ትሆኑ ዘንድ ጠላቶቻችሁን ውደዱ፤ የሚረግሟችሁን መርቁ፤ ለሚጠሉአችሁም መልካም አድርጉ፤ ስለሚያሳድዱ ችሁም ጸልዩ እርሱ በክፉዎችና በበጎዎች ላይ ፀሐይን ያወጣልና፤ በጻድቃንና በኃጢያተኞችም ላይ ዝናቡን ያዘንባልና።" (ማቴ. 5፡44) በ1ቆሮ. 13 ውስጥ የምናነበው ፍቅር ይህ መንፈስ ቅዱስ በልባችን ያፈሰሰው ዓይነት ነው።

<u>የውይይት መነሻ ጥያቄዎች</u>

1. የፍቅሩ ምንጭ ከሆንን ይህ ምንጭ እንደሚገባ እንዲፈልቅ ምን ማድረግ አለብን?

- ♦ __________
- ♦ __________
- ♦ __________
- ♦ __________
- ♦ __________

2. ምንጨን በንጽህና ለመጠበቅ ለምን አስፈላጊ ሆነ?

- 
- 
- 
- 
- 

## 30. ድንጋዩን ልብ አውጥቶ የሥጋን ልብ ሰጥቶሃል

"በትዕዛዜም ይሄዱ ዘንድ ፍርዴንም ይጠብቁና ያደርጉ ዘንድ አንድ ልብ እሰጣቸዋለሁ፤ በውስጣቸውም አዲስ መንፈስ እሰጣለሁ፤ ከሥጋቸውም ውስጥ የድንጋዩን ልብ አወጣለሁ፤ የሥጋንም ልብ እሰጣቸዋለሁ፤ እነርሱም ሕዝብ ይሆኑኛል እኔም አምላክ እሆናቸዋለሁ።" (ሕዝ. 11፡19-20፤ ሕዝ. 36፡26-27)

"ከክፉ ሕሊና ለመንጻት ልባችንን ተረጭተን ሰውነታችንንም በጥሩ ውኃ ታጥበን በተረዳንበት እምነት በቅን ልብ እንቅረብ።" (ዕብ. 10፡22)

ድንጋይ ጠንካራ ስለሆነ የሚወደቀበትን ነገር ሁሉ አንጥሮ ይመልሳል እንጂ ወደ ውስጥ አያስገባውም። የተፈጥሮ ልባችንም እንዲሁ ነው። የእግዚአብሔርን ነገር አይሰማም፤ አይቀበልም። ወደ ጌታ በምንመጣበትም ጊዜ መንፈስ ቅዱስ ጠንካራውን ልብ ይቀይርና የእርሱን ድምፅ የሚሰማ ለቃሉም የሚታዘዝ ልብ ይሰጠናል። የዚህን አስፈላጊነት ስለ አወቀ ነበር ዳዊት "አቤቱ ንጹሕ ልብን ፍጠርልኝ፤ የቀናውንም መንፈስ በውስጤ አድስ።" (መዝ. 50፡10) ያለው።

### የውይይት መነሻ ጥያቄዎች

1. የእግዚአብሔር ልብ በምን በምን ይታወቃል?

- 
- 
- 

♦
♦

2. የእግዚአብሔር ልብ ለምን ያስፈልጋል?

♦
♦
♦
♦
♦

3. ርኅራኄ የምን ፍሬ ነው?

♦
♦
♦
♦
♦

## 31. ዓለም የማትሰጠውን ሰላሙን ሰጥቶሃል

"ሰላምን እተውላችኋለሁ፤ ሰላሜን እሰጣችኋለሁ፤ እኔ የምሰጣችሁ ዓለም እንደሚሰጥ አይደለም።" (ዮሐ. 14፥27)

"እርሱ ሰላማችን ነውና..." (ኤፌ. 2፥14)

"ከዛሬ ጀምሮ እስከ ዘላለም ድረስ በፍርድና በጽድቅ ያጸናውና ይደግፈው ዘንድ በዳዊት ዙፋንና በመንግሥቱ ላይ አለቅነቱ ይበዛል፤ ለሰላሙም ፍጻሜ የለውም።" (ኢሳ. 9፥7)

"አዕምሮን ሁሉ የሚያልፍ የእግዚአብሔር ሰላም ልባችሁንና አሳባችሁን በክርስቶስ ኢየሱስ ይጠብቃል።" (ፊል. 4፥7)

ይህ ሰላም በሰላም አለቃና ለሰላሙ ፍጻሜ በሌለው በክርስቶስ ኢየሱስ የተሰጠን ስለሆነ ምንም ነገር ሊወስደው አይችልም። ይህ ሰላም ልብን የሚያሳርፍ፤ አዕምሮን ጸጥ የሚያደርግና ከእግዚአብሔር ዙፋን የሚመጣ ሰላም ነው። በዚህ ሰላም ውስጥ ሆነን ነው የእርሱን ታላቅነት የምናየው። ይህ ሰላም የሕይወትን ማዕበል ሁሉ ጸጥ የሚያደርግ መለኮታዊ ሰላም መሆኑን

ቃሉ ሲመሰክር እንደዚህ ይላል፦ "በአንተ ታምናለችና በአንተ ለምትደገፍ ነፍስ ፈጽመህ በሰላም ትጠብቃታለህ።" (ኢሳ. 26፥3)

## <u>የውይይት መነሻ ጥያቄዎች</u>

1. ከትንሣኤ በኋላ ከሁሉም ነገር በፊት ሰላም ለእናንተ ይሁን ያላቸው ለምንድነው?

- 
- 
- 
- 
- 

2. ያለ እግዚአብሔር ሰላም ሊኖረን ይችላልን?

- 
- 
- 
- 
- 

3. የሰላም ጠንቆች ምንድን ናቸው?

- 
- 
- 
- 
- 

## 32. የነፍስ እረፍት ሰጥቶሃል

"እናንተ ሸክማችሁ የከበደ ሁሉ ወደ እኔ ኑ፤ እኔም አሳርፋችኋለሁ።" (ማቴ. 11፥28)

የሚከብደንንና በሰው አቅምና ጉልበት ልንሸከም የማንችለውን ሸክማችንን ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ስለ ተሸከመልን እኛ የአዕምሮን ሰላም ብቻ ሳይሆን የነፍስንም እረፍት አግኝተናል። ልጆች ከሆንን ጥሪው ወደ እርሱ መጥተን የነፍስን እረፍት በመቀበል በእረፍት የመኖር ትርጉም የዋህና ትሁት ከሆነ ጌታ እንድንማር ነው። ማረፍን

እንኳን ባናውቅ ወደ እርሱ ከመጣን እርሱ ራሱ ማረፍን ያስተምረናል። ይህ ከሚመጣው ነገር ሁሉ ስጋት ነጻ መሆን ነው። "የሚሰማኝ ግን በእርጋታ ይቀመጣል፤ ከመከራም ሥጋት ያርፋል።" (ምሳ. 1፡33) በዚህ ዓይነት እረፍት ውስጥ ሆነን ነው የእግዚአብሔርን ታላቅነት ለማየት የምንችለው። "ዕረፉ እኔም አምላክ እንደ ሆንኩ ዕወቁ በአሕዛብ ዘንድ ከፍ ከፍ እላለሁ፤ በምድርም ላይ ከፍ ከፍ እላለሁ።" (መዝ. 45፡10)

## የውይይት መነሻ ጥያቄዎች

1. የነፍስ ዕረፍት ምንድነው?

- ◆ ______
- ◆ ______
- ◆ ______
- ◆ ______
- ◆ ______

2. ለነፍሳችን ዕረፍት ጠንቁ ምንድነው?

- ◆ ______
- ◆ ______
- ◆ ______
- ◆ ______
- ◆ ______

## 33. ጸድቀሃል

"እንግዲህ ወንድሞች ሆይ በእርሱ በኩል የኃጢአት ስርየት እንዲነገርላችሁ በሙሴም ሕግ ትጸድቁበት ዘንድ ከማይቻላችሁ ሁሉ ያመነ ሁሉ በእርሱ እንዲጸድቅ በእናንተ ዘንድ የታወቀ ይሁን።" (ሐዋ. 13፡39)

ጌታን ከተቀበልንበት ደቂቃ ጀምሮ በእግዚአብሔር ፊት ጻድቃን ሆነን ተቆጥረናል። የጸደቅነውም፦

33.1 በጸጋው ነው። "ከወደደን ከትልቅ ፍቅሩ የተነሣ በበደላችን እንኳ ሙታን በሆንን ጊዜ ከክርስቶስ ጋር ሕይወትን ሰጠን፤... ይህም የእግዚአብሔር ስጦታ ነው እንጂ ከእናንተ አይደለም" (ኤፌ. 2፡5፤8)

33.2 በእምነት ነው። "እንግዲህ በእምነት ከጸደቅን በእግዚአብሔር ዘንድ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ሰላምን እንያዝ፤" (ሮሜ 5፡1) እንዲሁም ገላ. 3፡24 ተመልከት።

33.3 በክርስቶስ ደም ነው። "ይልቁስ እንግዲህ አሁን በደሙ ከጸደቅን በእርሱ ከቁጣው እንድናለን።" (ሮሜ 5፡9)

33.4 በመንፈስ ቅዱስ ነው። "ያን መንፈስም፤ በጸጋው ጸድቀን በዘላለም ሕይወት ተስፋ ወራሾች እንድንሆን በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በእኛ ላይ አትርፎ አፈሰሰው። ቃሉ የታመነ ነው።" (ቲቶ 3፡6–7)

33.5 በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ነው። "ከእናንተም አንዳንዶቹ እንደ እነዚህ ነበራችሁ፤ ነገር ግን በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም በአምላካችንም መንፈስ ታጥባችኋል፤ ተቀድሳችኋል፤ ጸድቃችኋል።" (1ቆሮ. 6፡11)

## የውይይት መነሻ ጥያቄዎች

1. መጽደቅ ማለት ምን ማለት ነው?

- ______________________
- ______________________
- ______________________
- ______________________
- ______________________

2. "መጽደቅ የነጻነት ምልክት ነው" ስንል ምን ማለታችን ነው?

- ______________________
- ______________________
- ______________________
- ______________________
- ______________________

3. ይህ ዓይነት ነጻነት ከምን ነጻ መሆን ነው?

- ♦ ______________________________
- ♦ ______________________________
- ♦ ______________________________
- ♦ ______________________________

## 34. ተቀድሰሃል (ቅዱስ ነህ)

“ከእናንተም አንዳንዶቹ እንደ እነዚህ ነበራችሁ ነገር ግን በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ስም በአምላካችን መንፈስ ታጥባችኋል፤ ተቀድሳችኋል፤ ጸድቃችኋል፤” (1ቆሮ. 6፡11)

“...በክርስቶስ ኢየሱስ ለተቀደሱት የእነርሱና የእኛ ጌታ የሆነውን የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ስም በየስፍራው ከሚጠሩት ሁሉ ጋር ቅዱሳን ለመሆን ለተጠሩት፤” (1ቆሮ. 1፡2)

መቀደስ ማለት ለእግዚአብሔር መለየት ማለት ስለሆነ፤ ከጸደቅንበት ጊዜ ጀምሮ እግዚአብሔር የቅድስናውን ሥራ በእኛ ውስጥ እየሠራ ነው። ይህ በሕይወት እስካለን ድረስ የማያቋርጥ ሥራ ነው። (1ተሰ. 5፡23) እግዚአብሔር የቅድስናን ሥራ በእኛ ውስጥ የሚሠራው፦

34.1 በመንፈስ ቅዱስ ነው። “ነገር ግን አሕዛብ በመንፈስ ቅዱስ ተቀድሰው የተወደደ መስዋዕት ሊሆኑ፤ ለእግዚአብሔር ወንጌል እንደ ካህን እያገለገልሁ፤ ለአሕዛብ የክርስቶስ ኢየሱስ አገልጋይ እሆን ዘንድ ከእግዚአብሔር በተሰጠኝ ጸጋ ምክንያት ተመልሼ ላሳስባችሁ ብዬ በአንዳንድ ቦታ በድፍረት ጻፍሁላችሁ።” (ሮሜ 15፡16) እንዲሁም 1ጴጥ. 1፡2 ተመልከት።

34.2 በክርስቶስ ነው። “በቆሮንቶስ ላለች ለእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን፤ በክርስቶስ ኢየሱስ ለተቀደሱት፤ ለእነርሱና የእኛ ጌታ የሆነውን የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ስም በየስፍራው ከሚጠሩት ሁሉ ጋር ቅዱሳን ለመሆን ለተጠሩት።” (1ቆሮ. 1፡2)

34.3 በቃሉ ነው። "አሁንም እግዚአብሔር ያንጻችሁ ዘንድ በቅዱሳንም ሁሉ መካከል ርስትን ይሰጣችሁ ዘንድ ለሚችል ለጸጋው ቃል አደራ ሰጥቻችኋለሁ።" (ሐዋ. 20፡32)

34.4 በእምነት ነው። "የኃጢያትም ስርየት በእኔም በማመን በተቀደሱት መካከል ርስትን ያገኙ ዘንድ፤" (ሐዋ. 26፡17) እንደ ክርስቶስ ፈቃድ በመንፈስ ቅዱስ ምሪት በቅድስና እንደ ቃሉ መኖር ያለብን ለዚህ ነው። የቅድስናን አስፈላጊነት ሲናገር የጌታ ቃል እንዲህ ይላል፦ "ከሰው ሁሉ ጋር ሰላምን ተከታተሉ ትቀደሱም ዘንድ ፈልጉ፤ ያለ እርሱ ጌታን ሊያይ የሚችል የለምና።" (ዕብ. 12፡14)

## የውይይት መነሻ ጥያቄዎች

1. መቀደስ የምን ምልክት ነው?

◆ __________
◆ __________
◆ __________
◆ __________
◆ __________

2. ከምንድን ነው የምንለየው?

◆ __________
◆ __________
◆ __________
◆ __________
◆ __________

3. ለምንድን ነው የምንለየው?

◆ __________
◆ __________
◆ __________
◆ __________
◆ __________

## 35. ክርስቶስን እንድትመስል ወስኖሃል

“ልጁ በብዙ ወንድሞች መካከል በኩር ይሆን ዘንድ፣ አስቀድሞ ያወቃቸውን፣ የልጁን መልክ እንዲመስሉ አስቀድሞ ደግሞ ወስኖአልና፣ አስቀድሞ የወሰናቸውን እነዚህን ደግሞ ጠራቸው፤ የጠራቸውን እነዚህን ደግሞ አጸደቃቸው፣ ያጸደቃቸውን እነዚህን ደግሞ አከበራቸው።” (ሮሜ 8፥29)

“የዚያንም የመሬታዊውን መልክ እንደ ለበስን የሰማያዊውን መልክ ደግሞ እንለብሳለን።” (1ቆሮ. 15፥49)

እግዚአብሔር በራሱ መልክና አምሳል ነበር የፈጠረን ነገር ግን ያ በኃጢአት ምክንያት ስለ ተበላሸ የእርሱን መልክ እንድንመስል በክርስቶስ ኢየሱስ ደም አጥቦ አነጻን። ዕቅዱና ውሳኔው የክርስቶስ መልክ በኛ ውስጥ እንዲታይ ነው። ይህ ማለት ክርስቶስ አብን ለዓለም እንዳሳየ፣ (ዮሐ. 14፥9) እኛ ደግሞ ክርስቶስን ለዓለም እንድናሳይ ነው።

### <u>የውይይት መነሻ ጥያቄዎች</u>

1. የእግዚአብሔር ቀዳሚ ጥሪው ምንድነው?

♦ ____________________

♦ ____________________

♦ ____________________

♦ ____________________

♦ ____________________

2. አገልግሎት ከየት ይጀምራል?

♦ ____________________

♦ ____________________

♦ ____________________

♦ ____________________

♦ ____________________

3. ክርስቶስን የምንመስለው በምንድን ነው?

♦ ____________________

♦ ____________________

♦ ____________________

♦ ____________________

# 36. የክርስቶስ ክብር ማንጸባረቂያ ሆነሃል

"እኛም ሁላችን በመጋረጃ በማይከደን ፊት የጌታን ክብር እንደ መስተዋት እያብለጨለጭን መንፈስ ከሚሆን ጌታ እንደሚደረግ ያን መልክ እንመስል ዘንድ ከክብር ወደ ክብር እንለወጣለን።" (2ቆሮ. 3፥18)

"...ሙሴም ከተራራው በወረደ ጊዜ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ስለ ተነጋገረ የፊቱ ቁርበት እንዳንጸባረቀ አላወቀም ነበር።" (ዘጸ. 34፥29)

"በሸንጎም የተቀመጡት ትኩር ብለው ሲመለከቱት እንደ መልአክ ፊት ሆኖ ፊቱን አዩት።" (ሐዋ. 6፥15)

ሙሴ የእግዚአብሔርን ክብር እንደ መስተዋት እንዳንጸባረቀ እኛም የእርሱን ክብር ማለትም ቅድስናውን፤ ጽድቁን፤ ፍቅሩን፣ ርኅራኄውን፤ ቸርነቱንና የመሳሰሉትን ሁሉ ለሌሎች እንድናንጸባርቅ መንፈስ ቅዱስ በልባችን ውስጥ ይሠራል። ይህን የሚያስችለን ኃይል ከእርሱ የሚመጣ ሲሆን ፈቃደኛነቱ ከእኛ ይጠበቃል። "ነገር ግን የኃይሉ ታላቅነት ከእግዚአብሔር እንጂ ከእኛ እንዳይሆን..." (2ቆሮ. 4፥7)

## የውይይት መነሻ ጥያቄዎች

1. የክብሩ ማንጸባረቅ ማለት ምን ማለት ነው?

- ◆ ______
- ◆ ______
- ◆ ______
- ◆ ______
- ◆ ______

2. ክብሩን ለማንጸባረቅ ምን ይጠበቅብናል?

- ◆ ______
- ◆ ______
- ◆ ______
- ◆ ______
- ◆ ______

## 37. እግዚአብሔር በአንተ ደስ ብሎታል

"ነገር ግን እግዚአብሔር ባንቺ ደስ ብሎታልና..." (ኢሳ. 62፥4)

"አምላክሽ እግዚአብሔር በመካከልሽ ታዳጊ ኃይል ነው፤ በደስታም በአንቺ ደስ ይለዋል፤ በፍቅሩም ያርፋል፤ በእልልታም ባንቺ ደስ ይለዋል ይባላል።" (ሶፎ. 3፥17)

"በዚያን ሰዓት ኢየሱስ በመንፈስ ቅዱስ ሐሴት አደረገና፦ የሰማይና የምድር ጌታ አባት ሆይ፥ ከጥበበኞችና ከአስተዋዮች ሰውረህ ለሕጻናት ስለ ገለጥህላቸው አመሰግንሃለሁ፤ አዎን አባት ሆይ ፈቃድህ በፊትህ እንዲህ ሆኖአልና።" (ሉቃ. 10፥21)

"እግዚአብሔር በቃል ኪዳኑ የታመነ ነው፤ እርሱ የሚያደርገው ሁሉ መልካም ነው።" (መዝ. 145፤13 አዲሱ ትርጉም)

<u>የውይይት መነሻ ጥያቄዎች</u>

1. እግዚአብሔር በቃል ኪዳን ከተቀበለን እንዴት መኖር ይገባናል?

- ______
- ______
- ______
- ______
- ______

2. እግዚአብሔር በአንተ ከተደሰተ የአንተ ሃላፊነት ምንድነው?

- ______
- ______
- ______
- ______
- ______

3. "በጌታ ደስ ይበላችሁ" የሚለው ቃል ከዚህ ጋር ምን ግንኙነት አለው?

- ______
- ______
- ______
- ______
- ______

4. "ጌታ በደስታ ዘይት ይቀባሀ" ሲል ምን ማለቱ ነው? (ኢሳይ. 61:1-3)

- ◆ ______
- ◆ ______
- ◆ ______
- ◆ ______
- ◆ ______